# ወንጌላት

ትምህርት
ሁለት

## የማቴዎስ ወንጌል

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM
MINISTRIES
Biblical Education. For the World. For Free.

© 2012 by Third Millennium Ministries

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form or by any means for profit, except in brief quotations for the purposes of review, comment, or scholarship, without written permission from the publisher, Third Millennium Ministries, Inc., P.O. Box 300769, Fern Park, Florida 32730-0769.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

**አስተዋፅዖ**


1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**

   ሀ. ጸሐፊው

      1. ትውፊታዊው አመለካከት
      2. ግላዊ ታሪክ

   ለ. ቀደምት ተደራሲያን

   ሐ. ወቅት

      1. ቀን
      2. ስፍራ
      3. ዓላማ

3. **አወቃቀርና ይዘት**

   ሀ. መግቢያ፡ መሲሐዊ ንጉሥ

      1. ትውልድ
      2. የልጅነት ታሪክ

   ለ. የመንግሥት ወንጌል

      1. መሲሑ መጥቷል
      2. የተራራው ስብከት

   ሐ. የመንግሥቱ መስፋፋት

      1. የኢየሱስ ተዓምራትና ምላሹ
      2. የንጉሡ አምባሳደሮች

   መ. ምልክቶችና ምሳሌዎች

      1. ምልክቶችና ምላሻቸው
      2. የመንግሥቱ ምሳሌዎች

   ሠ. እምነትና ትልቅነት

      1. በኢየሱስ ማመንን መቃወም
      2. ታላቅነት በመንግሥቱ ቤተሰብ ውስጥ

   ረ. የአሁን ተቃውሞና የወደፊት ድል

1. ብርቱ ተቃውሞ
2. የወደፊት ድል

ሰ. የኢየሱስ አገልግሎት መደምደሚያ

1. ግጭት
2. ደቀመዝሙርነት
3. ድል

## 4. ዐቢይ ሃሳቦች

ሀ. የብሉይ ኪዳን ቅርስ

1. ጥያቄዎችና ጉምጉምታ
2. መንግሥተ ሰማያት
3. መሲሐዊ ንጉሥ
4. የማያምኑ የአይሁድ መሪዎች
5. ትኅትናና ገርነት

ለ. የእግዚአብሔር ህዝብ

1. ቤተክርስቲያን
2. የእግዚአብሔር ቤተሰብ
3. ጥሪ

## 5. ማጠቃለያ

# መግቢያ

የቤልጂየሙ ንጉሥ አልበርት በ1919 ዓ.ም. ዩናይትድ ስቴትስን በባቡር ዞሯት ነበር። በጎታቹ ክፍል ውስጥ ሥልጣን ያለው ሰው ሆኖ ነበር፣ ስለዚህም ለ0ሥር ማይሎች ያህል እንደ ኢንጂነር ለብሶ ባቡሩን ነዳ። በሚቀጥለው ፌርማታ፣ በአድናቆት የተሞላው ህዝብ ንጉሥ አልበርትን ቢጠብቅም አላገኘውም። ንጉሥ ሊመስልና ሊያደርግ ይገባል የሚሉበት መንገድ ነበራቸው። ስለዚህም፣ ረጅሙና የፍላኔል ሸሚዝና የባቡር መንገድ ኮፍያ የለበሰው ሰው በእውነት የቤልጅየም ንጉሥ ነው ብለው አላመኑም።

በአንድ ወገኑ፣ የማቴዎስ ወንጌልም የሚነግረን ተመሳሳይ ታሪክ ነው። ስለ አይሁድ ንጉሥ ስለ ኢየሱስ የሚናገር ታሪክ ነው። በእርሱ ዘመን ያሉ ብዙዎች ግን አላወቁትም ምክንያቱም ሰዎች ይሆናል ብለው እንደሚጠብቁት አልነበረም ደግሞም ሰዎች እንደሚጠብቅትም አያደርግም ነበር። እርሱ ለየት ያለ ንጉሥ ነበር።

ወንጌላት ከተባለው ተከታታይ ትምህርታችን ይህ ሁለተኛው ነው። ይህንንም "**የማቴዎስ ወንጌል**" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፣ ምክንያቱም የምናተኩረው በወጀመሪያው ወንጌል፣ በማቴዎስ መጽሐፍ ላይ ስለሆነ ነው።

የማቴዎስ ወንጌል ጥናታችን በሦስት የተከፈለ ነው። አንደኛ፣ የማቴዎስን መጽሐፍ ዳራ እናያለን። ሁለተኛ፣ መዋቅሩንና ይዘቱን እንመረምራለን። ሦስተኛ ደግሞ፣ በማቴዎስ ወንጌል የሚገኙ አንዳንድ ዋና ርዕሶችን እንመለከታለን።

# ዳራ

*በርካታ ሰዎች "ስለ መጽሐፍ አውዳዊ ትንታኔዎችን ማወቅ ለምን ያስፈልገኛል? ጥሩ የሆነ የአማርኛ ትርጉም ፈልጌ ማንበብና ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ አይበቃኝምን?" በማለት ይጠይቃሉ። አውድ የሌለው ምንባብ፣ ምንባቡ ምን ሊል እንደፈለገ ከመረዳት አንፃር ቅድመ ምንባብ ብቻ ነው። ችግሩ ጥንታውያን ፅሁፎች ታሪካዊ፣ ስነ-ፅሁፋዊ፣ የአነጋገር ዘይቤያዊ፣ ከርሰ ምድራዊ፣ እና ሃይማኖታዊ አውዶች አሏቸው፤ እነዚያም አውዶች ከእኛ ፍፁም የተለዩ ናቸው። አንድ ሰው በአንድ ወቅት "ያለፈው ነገር ባዕድ ነው፣ ነገሮችን በተለየ መንገድ ያደርጉ ነበርና" ብሏል። ያለፈው ከአሁኑ እጅግ የተለየ ነው፣ የእኛን ዘመን ግምቶች ይዘን የቀደሙትን ለማንበብ የመሞከራችን ዘመንን ያለመገንዘብ ግርዶሽ የምናስወግደው አውዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማድረግ ነው። [ዶ/ር ቤን ዊተሪንግተን]*

*አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ በምንተረጉም ወቅት በትክክል ለመፍታት የጸሐፊውን ማንነትና ታሪካዊ አውዱን የሚዳስሱ ዳራዎችን መረዳት ያስፈልገናል ምክንያም ጸሐፊዎች መጽሐፍ ሲጽፉ፣ ተደራሲያኖቻቸው የጋራ በሆነ ባህል ውስጥ እንዳሉና የሚጽፉትንም ሃሳብ*

*ሰፊ አውድ ይረዳሉ ብለው ያስባሉ፡፡ እናም የእኛ ተግባር በብዙ መንገድ፣ ጸሐፊው ማን እንደነበረ፣ ባህሉ ምን እንደነበረ፣ መለየትና ከሰፊው ባህልና ታሪክ ብርሃንን ማግኘት ይሆናል፡፡ ያን ጊዜም እነዚያን መረጃዎችና እውነታዎች በውል እናስቀምጣለን፡፡ [ዶ/ር ጀምስ ሃሚልተን]*

የማቴዎስን ወንጌል ዳራ በሦስት እርከኖች እንወያይበታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ማቴዎስ እንደጻፈው እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ማቴዎስ ቀደምት ተደራሲያን እንነጋገራለን፡፡ ሦስተኛ፣ ማቴዎስ የጻፈበትን ወቅትና ሁኔታዎች እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን በወንጌሉ ጸሐፊ ማንነት ላይ የሚነሳውን ጥያቄ እንመልከት፡፡

## ጸሐፊ

አንድን መጽሐፍ፣ ደብዳቤ ወይም ማንኛውንም ፅሑፍ ስናነብብ፣ ፀሐፊውን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሠረቱ፣ ስለ ፀሐፊውና ስለ አውዱ ብዙ ባወቅን መጠን፣ የእርሱን አመለካከቶችና ትርጓሜዎች በተሻለ መንገድ ለመረዳት ዝግጁዎች እንሆናለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስንም ስናነብብ ይህ እውነት የተጠበቀ ነው፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፍት ይበልጥ ባወቅን መጠን፣ የሚያስተምሩንን ነገር በተሻለ መንገድ ለመረዳት ዝግጁ እንሆናለን፡፡ ስለዚህ፣ ወደ ማቴዎስ ወንጌል ስንመጣ፣ ልንጠይቅ ከሚያስፈልጉን ጥያቄዎች አንዱ "**ይህን መጽሐፍ ማን ፃፈው**?" የሚለው ነው፡፡

የማቴዎስን ወንጌል ጸሐፊ በሁለት ደረጃዎች እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ይህ ወንጌል ከዐሥራ ሁለቱ ቀደምት የኢየሱስ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ሐዋርያው ማቴዎስ ፅፎታል የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት እናፀናለን፡፡ ሁለተኛ፣ የማቴዎስን ግላዊ ታሪክ እንመረምራለን፡፡ እስኪ የወንጌሉ ፀሐፊ ማቴዎስ ነው የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት በመመልከት እንጀምር፡፡

## ትውፊታዊ አመለካከት

*ምንም እንኳን አሁን አሁን አንዳንድ ምሁራን ቢጠራጠሩም፣ ሐዋርያው ማቴዎስ፣ የማቴዎስ ወንጌል ፀሐፊ መሆኑን የሚያረጋግጡልን በርካታ መተማመኛዎች አሉን ብዬ አስባለሁ፡፡ አንዱ፣ ቀደምት የቤተክርስቲያን አባቶች በጣም ተጠራጣሪዎች ነበሩ፣ ስለዚህም ተዓማኒነት የሌላቸውን አስመሳዮች የመቃወማቸውን፣ እስትንፋሰ መለኮት በሆኑት በቅዱሳት መጻሕፍት ካኖናዊ ሥራ ውስጥ ባለማካተቱ ረገድ የነበራቸውን ጥንቃቄ ማቃለል ነው፡፡ ሁለተኛ፣ የማቴዎስን ፀሐፊነት አስመልክቶ ሌላ አንድም ተፎካካሪ ትውፊት አለመኖሩ ነው፡፡ ብቸኛው ትውፊት መጽሐፉን ማቴዎስ እንደፃፈው የሚነገረው ነው፡፡ ሦስተኛ፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያን ያለምንም ታሪካዊ ምክንያት የዚህን ወንጌል መጠሪያ ከሐዋርያት ለአንዱ ሰጠች ብለን ብንል፣ ምርጫቸው እጅግ ደካማ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ማቴዎስ ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር፡፡ ሙያው በአይሁድ ዘንደ የተናቀ ነበር፡፡ የማቴዎስ ወንጌል ደግሞ አይሁድን ተደራሲ ያደረገ፣ ኢየሱስም መሲሁ መሆኑን ሊያሳምናቸው የሚጥር ወንጌል ነው፡፡ ታዲያ ኢየሱስን መሲሁ ነው ብሎ አይሁድን ለማሳመን የተፃፈን ወንጌል፣ ብድግ ብለው ለማቴዎስ ሰጡት ብሎ ማሰብ ትርጉም የለሽ ነው፡፡ የማቴዎስን ወንጌል ከማቴዎስ ስም ጋር ያገናኙበት ብቸኛው*

*ምክንያት፣ ማቴዎስ ስለ መፃፉ መልካም እና ጠንካራ ምክንያት እንዳለ ማመናቸው ነው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ኮዋን]*

የመጀመሪያውን ወንጌል ማቴዎስ ፅፎታል የሚለው ትውፊት የመጣው በቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ምዕተ ዓመት ነው፡፡ በሁሉም ጥንታዊና ስም በተሰጣቸው የዚህ ወንጌል ቅጂዎች ውስጥ፣ የፀሐፊነቱ ሥልጣን የተሰጠው ለማቴዎስ ብቻ ነው፡፡ ይህ ወንጌል በአብያተ ክርስቲያናት በሚዘዋወርበት ወቅት ከማቴዎስ በስተቀር ሌላ ስም ተሰጥቶት አያውቅም፡፡

የመጀመሪያውን ወንጌል ለማቴዎስ ከመስጠት አንፃር ቀዳሚ የሚሆነው የሄራፖሊሱ ፓፒያስ ነው፡፡ የኖረውም ከመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ማብቂያ እስከ እስከ ሁለተኛው ማብቂያ ድረስ ነው፡፡ እኛ ካገኘናቸው ሁሉ የቀደምት ቤተክርስቲያንን አመለካከት የሚወክል ነበር፡፡

የቤተክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊው የቂሳርያው ዮሲበስ በ325 ዓ.ም. አካባቢ Ecclesiastical History በተሰኘው 3ኛ መጽሐፍ 39 ክፍል 16 ውስጥ የማቴዎስ ወንጌልን ፀሐፊ አስመልክቶ የፓፒያስን ምስክርነት ዘግቧል፡፡ የፓፒያስን ቃል አድምጡ፡

***ማቴዎስ ቃሉን በቅደም ተከተል አስፍሮታል፡፡***

በሁለተኛው ምዕተ ዓመት፣ ፓፒያስ የወንጌሉን ፀሐፊነት ለማቴዎስ መስጠቱን እንመለከታለን፡፡ ዮሲበስም የእርሱን አመለካከት ከፓፒያስ ጋር በማጣጣም የመጀመሪያው ወንጌል ፀሐፊ ማቴዎስ መሆኑን ማረጋገጡን መጥቀሱ አግባብነት አለው፡፡

ሌላው ቀደምት የቤተክርስቲያን አባት ደግሞ የሊዮኑ ኢራኒየስ ሲሆን፣ በ180 ዓ.ም. አካባቢ Against Heresies በተሰኘው 3፥1 መጽሐፉ ክፍል አንድ ውስጥ የመጀመሪያውን ወንጌል ለማቴዎስ ሰጥቷል፡፡

***ጴጥሮስና ጳውሎስ በሮሜ ሲሰብኩ እና የቤተክርስቲያንን መሠረት ሲያኖሩ፣ ማቴዎስም የተፃፈውን ወንጌል ለአይሁድ በቋንቋቸው ያቀርብ ነበር፡፡***

ተርቱሊያንከ115 – 230 ቀደም ብሎ የኖረ ነው፡፡ Against Marcion በተሰኘው 4ኛ መጽሐፉ ምዕራፍ 2 ውስጥ፣ የማቴዎስን ፀሐፊነት አረጋግጧል፡፡

***ከሐዋርያት ሁሉ፣ በቀደምትነት እምነትን በውስጣችን ያሳደሩት ዮሐንስና ማቴዎስ ሲሆኑ .... ሉቃስና ማርቆስ ቆየት ብለው አድሰውታል፡፡***

ተርቱሊያንንና ኢራኒየስም፣ ማቴዎስ ፅፎታል ብለዋል፡፡ ይህም አቋማቸው በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የማቴዎስ የመጀመሪያው ወንጌል ፀሐፊነት በእርግጠኝነት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የማቴዎስን ጸሐፊነት የሚናገሩት ቀደምት ማረጋገጫዎች የበለጠ የተጠናከሩት የማቴዎስ ጸሐፊነት በማጠራጠሩ አንፃራዊነት ምክንያት መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ወይንም አንድ ግለሰብ በራሳቸው ምርጫ የጸሐፊነቱን ሥልጣን ከሐዋርያት ለአንዱ በመስጠት ወንጌሉን

ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ ከፈለጉ፣ ከሐዋርያት ዋነኛ የሆነውን መምረጣቸው አያጠራጥርም፡፡ ማቴዎስ ግን በወንጌላቱ የተጠቀሰው አልፎ አልፎ ነው፡፡ ይህም ስሙ ከወንጌሉ ጋር በተሳሳተ መንገድ ተያይዟል የሚል መላ ምት እንዲኖር አድርጓል፡፡

> *ከሁሉ አስቀድሞ፣ በመጀመሪያው ክፍለ መን የዐይን ምስክር ምስክርነትን አስፈላጊነት እውቅና ልንሰጠው ይገባናል፡፡ የዐይን ምስክር ማረጋገጫ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ የዐይን ምስክርነት አለኝ የሚልን ሰው ማረጋገጫ ማቅለል ጨርሶ አይቻልም፡፡ የሆኑ ነገሮችን ሲሆኑ ዐይቶ መናገር እጅግ ተዓማኒ ከሆኑ ምድቦች የሚወሰድ ነው፡፡ በሁለተኛው ምዕተ-ዓመት የኖረውና የቅርቡ የነበረው ፓፒያስ የማቴዎስን ወንጌል ሐዋርያው ማቴዎስ ጽፎታል ሲል ጽፏል፡፡ ከኖረበት ዘመን ጋር ስናስተያየው ፓፒያስ ሐዋርያትን በቀጥታ ያውቃቸዋል፡፡ የማቴዎስ ወንጌል በሐዋርያው ማቴዎስ ተጽፏል በማለት በእርግጠኝነት የማቀርበው የመጨረሻው ምክንያት፣ ምንም እንኳን የማቴዎስ ስም በወንጌሉ ውስጥ ባይጠቀስም፣ የማቴዎስ ወንጌል ሐዋርያው ማቴዎስ እንደጻፈው ካልተጠቀሰ በስተቀር በዘመኑ ሊሰራጭ የማይችል መሆኑን ነው፡፡ [ቄስ ሚካኤል ግሉዶ]*

እርግጥ ነው፣ ዘመነኞቹ ፅጉር ሰንጣቂ ምሁራን በሌሎቹም ትውፊታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊነት ማረጋገጫዎች ላይ እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ የማቴዎስን የመጀመሪያውን ወንጌል ጸሐፊነትም ይጠራጠራሉ፡፡ ሆኖም የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ማቴዎስ ነው የሚለው ጥንታዊ የተጠናከረ ማረጋገጫ፣ በጥንት ዘመን ጸሐፊነቱን አስመልክቶ የቀረበ የጠነከረ ሙግት ካለመኖሩ ጋር ተጨምሮ ይህንን ወንጌል እርሱው ጽፎታል ብለን በብርቱ እንድናምን ያደርገናል፡፡

የመጀመሪያውን ወንጌል ማቴዎስ ጽፎታል የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት ከዳሰስን፣ አሁን ደግሞ ወደ ማቴዎስ የግል ታሪክ እንሸጋገራለን፡፡

## የግል ታሪክ

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ማቴዎስ የግል ታሪክ ጥቂት አስፈላጊ ጭብጦችን ያቀርቡልናል፡፡ ለምሳሌ፣ አይሁዳዊ ደግሞም ቀረጥ ሰብሳቢ እንደነበረም ይጠቅሳል፡፡ ሁለቱንም በጥልቀት እንመለከታለን፣ አስቀድመን ግን ከማቴዎስ አይሁዳዊነት እንጀምር፡፡

የማቴዎስ የአይሁድ ዝርያ የተጠቀሰው በብዙ መንገዶች ነው፡፡ አንደኛው፣ ሁሉም አይሁዳውያን ከነበሩት፣ ከኢየሱስ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር፡፡ ሌላኛው ደግሞ፣ ማቴዎስ የአይሁድ ስሞች ነበሩት፡፡ ማቴዎስ ራሱ የአይሁድ ስም ሲሆን፣ ከብሉይ ኪዳኑ ዕብራይስጥ የተወሰደ ነው፡፡ ሌላው ስሙ፣ ሌዊ ደግሞ፣ በማርቆስ 2፥14 እና ሉቃስ 5፥28 የምናገኘው ሲሆን፣ ከእስራኤል ነገዶች የአንዱ ስም ነው፡፡ እናም፣ ሁለቱም ስሞቹ ማቴዎስ አይሁዳዊ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም የማቴዎስ የአይሁድ ዝርያ እርሱው በእብራይስጥ በጻፋቸው ጥንታዊ ክርስቲያናዊ ዘገባዎችም ተገልጠዋል፡፡

የማቴዎስ የአይሁድ ተወላጅነት ወንጌሉን በትክክል ከመረዳት አንፃር ወሳኝ ነው ምክንያቱም የጠነከረ አፅንዖት የሰጠበትን አይሁዳዊ ትኩረቱን ለመተርጎም ያግዘናልና ነው፡፡ የዚህን ወንጌል

አይሁዳዊ ባህርይ ቆየት ብለን በዚሁ ትምህርት በጥልቀት እናየዋለን፡፡ ለአሁኑ ግን፣ ለገለጣ ያህል ብቻ አንድ ምሳሌ ብቻ እናነሳለን፡፡

በማቴዎስ 15፥24፣ ኢየሱስ የሚከተለውን እንደተናገረ ማቴዎስ ዘግቧል፡

> ***እርሱም መልሶ፡- ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ።*** (ማቴ 15፥24)

ኢየሱስ በተለይ ለእስራኤል መንግሥት የመጣ መሆኑን ከሌሎቹ ወንጌላት በበለጠ ማቴዎስ አፅንዖት በመስጠት ጽፏል፡፡

ከማቴዎስ አይሁድነት ባሻገር፣ ብዙም ፋይዳ የሌለው የሕይወቱ ክፍል ቀረጥ ሰብሳቢነቱ ነበር፡፡

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፣ በፓለስታይን የሚኖሩ በርካታ አይሁድ ለሮሜ መንግሥት ቀረጥ ይሰበስቡ ነበር፡፡ ከነዚህ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ጥቂቶቹ ከቦታ ቦታ በሚዘዋወሩ ሸቀጦች ላይ ታሪፎችን ይጥሉ ነበር፡፡ ቀረጥን የመሰብሰብ ሥልጣን ለሰጧቸው ገዢዎች ገንዘብ የሚከፍሉ የግል ተቋማት ነበሩ፡፡ ስለዚህ ከህዝብ የሚሰበስቡትን የቀረጥ መጠን በየጊዜው በማናር የራሳቸውን ትርፍ ይሰበስቡ ነበር፡፡ በውጤቱም፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎች እንደ መዝባሪና ቀማኛ ይቆጠሩ ነበር ይህም አብዛኛውን ጊዜ የተረጋገጠ ነበር፡፡

በዚህ ምክንያት፣ አይሁዳዊ ቀረጥ ሰብሳቢዎች በአገራቸው ሰዎች ዘንድ ድርብ ወንጀለኛ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር፡፡ በመጀመሪያ፣ የሚጠላው የሮም ወራሪ ወኪሎች በመሆናቸው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የራሳቸውን ህዝብ የሚመዘብሩ በመሆናቸው፡፡ እንዲየውም፣ በአይሁድ ችሎት ላይ ቀርበው ምስክርነት መስጠት የማይችሉ የማይታመኑ ክፉ ሰዎች እንደሆኑ ተደርገው በቀደምት የአይሁድ ፅሑፍት ዘንድ ይቆጠሩ ነበር፡፡ ከዚህም በላይ፣ ለቀረጥ ሰብሳቢዎች ውሸት የተፈቀደ እንዲያውም የሚመሰገን የስርቆት ዘዴ ነበር፡፡

እስኪ በማቴዎስ 9፥9-10 በኢየሱስ ስለመጠራቱ ማቴዎስ የመዘገበውን አድምጡ፡

> ***ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየና። ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው።***
> ***በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ እነሆ፥ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች መጥተው ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ተቀመጡ። (ማቴ 9፥9-10)***

ማቴዎስ ስለ ራሱ ሲናገር በፍጹም ግልፅነት ይናገራል፣ ኢየሱስ በኖረበትም ዘመን እርሱና ሌሎች ቀረጥ ሰብሳቢዎች "ከኃጢአተኞች" ጋር ይቆጠሩ እንደነበር በይፋ ይናገራል፡፡ ይህንንም በማድረጉ፣ ማቴዎስ ራሱን፣ ኢየሱስንና የጻፈውን ወንጌል ከአይሁድ መሪዎች ጋር በተቃራኒው ያስቀምጣቸዋል፡፡ ይህንን የመሰለው ክፍፍል በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 21፥31-32 ኢየሱስ የአይሁድን መሪዎች የነቀፈበትን መንገድ አድምጡ፡

*ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ቀራጮችና ጋለሞቶች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሙአችኋል። ዮሐንስ በጽድቅ መንገድ መጥቶላችሁ ነበርና፥ አላመናችሁበትም፤ ቀራጮችና ጋለሞቶች ግን አመኑበት፤ እናንተም ይህን አይታችሁ ታምኑበት ዘንድ በኋላ ንስሐ አልገባችሁም። (ማቴ 21፥31-32 )*

ማቴዎስ ስለ ግል የኃጢአተኝነት ታሪኩ በግልፅ ለመናገር የመፍቀዱ ነገር በዚህ ትምህርት ወደ ኋላ ላይ በጥልቀት ከምንዳስሰው ከወንጌሉ ሌላ አፅንዖት ጋር ሊዛመድ ይችላል፡፡ ከሌሎቹ የወንጌል ጸሐፍት በበለጠ መንገድ፣ ትሁት የሆነው ንጉ ኢየሱስ፣ ተከታዮቹን ወደ ትህትና የጠራ በመሆኑ ላይ አትኩሯል፡፡ ላለፈ ሕይወቱ እውቅና በመስጠት፣ እርሱ ራሱ ጸጋ የሚያስፈልገው መሆኑን በነፃነት የገለፀ ሲሆን፣ የጠራውንና የሞገተውን ንጉሥ ለመከተል ያለውንም ፈቃደኝነት አውጇል፡፡ ኢየሱስ እርሱን በኃጢአት ከረከሰው የሄሮድስ አገልጋይነት ወደ ትሁት የሰማይ መንግሥት ወንጌል አገልጋይነት ለውጦታል፡፡

*ትህትና በሕይወታችን ሊገለጥ የሚገባው፣ ለሰዎች በጎ ነገር ሲደረግላቸው ለእኛም እንዲሁ ሲደረግልን ደስ በመሰኘታችን፣ በመርካታችን፣ በተለይ ደግሞ ሰዎች በአንድ መንገድ ከበሬታን ሲያገኙ ወይንም ሥራቸው ፍሬያማ ሲሆን በዚያ ደስ በመሰኘታችን ነው፡፡ ስለዚያም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፣ ከሁሉ አስቀድመንም ጌታን ማክበርና ማመስገን እንፈልጋለን፡፡ ልንናገር የምንፈልገውም ስለ ራሳችን ብቻ ሳይሆን ከሁሉ በላይ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው፡፡ እንግዲያው ትህትና ማለት ያ ነው እንጂ የእኔ ፍላጎት የመሟላቱ ነገር አይደለም፡፡ ከሁሉ የሚቀድመው የእግዚአብሔር መሻት በእኔም ሆነ በሌላ ሰው በኩል የመሟላቱ ጉዳይ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆን ማኪንሌይ]*

የመጀመሪያውን ወንጌል ማቴዎስ ጽፎታል የሚለው ትውፊታዊ አመለካከት ትክክል መሆኑን ካረጋገጥን እና ጥቂት የግል ታሪኩን ካወቅን፣ አሁን ደግሞ ማቴዎስ የጻፈላቸውን የመጀመሪያ ተደራሲያን ማንነት እንመረምራለን፡፡

## የመጀመሪያ ተደራሲያን

ማቴዎስ ቀደምት ተደራሲያኑን በግልፅ አልነገረንም፣ ሆኖም ስለ እነርሱ ጥቂት ፍንጮችን ይሰጠናል፡፡ በኋላ እንደምናየው፣ ማቴዎስ በተቀዳሚነት የጻፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች ይመስላል፡፡

ቀደም ባለው ትምህርት፣ ሁሉም ወንጌላት የተጻፉት ለክርስቲያን ተደራሲያን መሆኑን ጠቅሰናል፡፡ ሆኖም በማቴዎስ ወንጌል የተቀመጡ የተለያዩ አጽንዖቶች አይሁዳዊ ዳራ ላላቸው ክርስቲያኖች የበለጠ የሚገጥም መሆኑን በውል ያሳዩናል፡፡ ለምሳሌ፣ ከሌሎቹ የወንጌል ፀሐፍት በበለጠ

ምቴዎስ ብሉይ ኪዳንን ጠቅሷል፡፡ ኢየሱስ እንዴት የብሉይ ኪዳንን ጥበቃዎች እንዳሟላ ደጋግሞ አመልክቷል፡፡ በተለይም ደግሞ ኢየሱስ አይሁድ ለብዙ ምዓተ-ዓመታት ሲጠብቁት የኖረው መሲሃዊ ንጉሥ መሆኑን በአፅንዖት ተናግሯል፡፡ ከማያምኑ የአይሁድ መሪዎች ጋር ኢየሱስ ያደረጋቸውን ግጭቶች ከሌሎቹ የወንጌላት ፀሐፍት በጠለቀ መንገድ ሲገልፃቸውም በአይሁድ ነክ ጉዳዮች ላይ የሰጠው አፅንዖት ይስተዋላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማቴዎስ ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን ህግ ጋር ባለው ግንኙነት፣ በተለይም የሕጉ ጌታ በመሆኑ ላይ ትልቅ ትኩረት አድርጓል፡፡

በዚህ ትምህርት ወደ ኋላ ላይ አንዳንዶቹን አፅንዖቶች በበለጠ ጥልቀት እንመለከታቸዋለን፡፡ ስለዚህ፣ አሁን፣ ማቴዎስ ለአይሁድ የጻፈ መሆኑን የሚያሳዩንን ሁለት ምሳሌዎች እናነሳለን፣ አስቀድመንም "***መንግሥተ ሰማያት***" የተሰኘውን የማቴዎስን አገባብ እንመለከታለን፡፡

ከደም ባለው ትምህርት፣ አራቱም ወንጌላት የእግዚአብሔር መንግሥት በተሰኘው መሪ ሃሳብ ላይ አንድ እንደሆኑ ጠቅሰናል፡፡ ማቴዎስ ግን "**የእግዚአብሔር *መንግሥት***" የሚለውን ሐረግ የተጠቀመው አልፎ አልፎ ነው፡፡ በምትኩ ግን ጥቅል በሆነ መንገድ "***መንግሥተ ሰማያት***" የሚለውን ሐረግ ተጠቅሟል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን ቃል የተጠቀመ ማቴዎስ ብቻ ነው፡፡ እንደተመለከትነው፣ ሁለቱም ሐረጎች የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው፡፡

አይሁድ ለእግዚአብሔር ካላቸው አክብሮት የተነሳ፣ መለኮታዊ ስሞችን ወይም ወደዚያ የቀረበ ስያሜ ከመጠቀም ይቆጠባሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ላለመጥራት ነው፡፡ ይህንን የሚያደርጉበት አንዱ መንገድ "**እግዚአብሔር**" የሚለውን ቃል "***መንግሥተ ሰማይ***" በሚለው መተካት ነው፡፡ በተመሳሳዮቹ ወንጌላት የተጠቀሱ ተጓዳኝ ምንባቦችን ስናስተያይ፣ ሌሎቹ ወንጌላት "**የእግዚአብሔር *መንግሥት***" በማለት የተጠቀሙበትን ማቴዎስ "***መንግሥተ ሰማያት***" በሚል ሐረግ ተክቶታል፡፡

> *በሌሎቹ ወንጌላት "**የእግዚአብሔር መንግሥት**" ተብለው የምናገኛቸውን ማጣቀሻዎች አብዛኛውን ጊዜ ማቴዎስ "**መንግሥተ ሰማያት**" በሚለው ሐረግ ተክቷቸው እናገኛለን፡፡ ማቴዎስ "**የእግዚአብሔር መንግሥት**" የሚለውን ሐረግ የተጠቀመባቸው ጊዜዎች እንደሚኖሩ አስባለሁ፣ ይህ የሆነው ግን ማቴዎስ አይሁዳዊ ጸሐፊ ቢሆንም፣ በክርስቶስ ያመነ አይሁድም ስለሆነ ነው፣ ለአይሁድ ግን፣ እግዚአብሔር የሚለው ስም በቀላሉ የማይጠቀሙበት እጅግ የተቀደሰ ስም ነው፡፡ ስለዚህም፣ "**መንግሥተ ሰማይ**" የሚለውን ሐረግ መጠቀም እግዚአብሔርን ለማመልከት ከሚጠቀሱ አገባቦች አንዱ ነው፡፡ በሌላ ወንጌል ውስጥ "**በሰማይም በምድርም በደልሁ**" ይህ ማለት "**እግዚአብሔርን በደልሁ**" ማለት ነው፡፡ አደጋው ግን "**መንግሥተ ሰማያት**" የሚለውን ሐረግ ስንሰማ፣ "**ኦ፣ይህማ በጣም መንፈሳዊና በዐይን የማይታይ ነው ... መንግሥተ ሰማያትን ማየት አንችልም**" በማለት አሳስተን ልንሰማ እንችላለን፡፡ በመሠረቱ፣ እርሱ እየተናገረ ያለው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲሆን፣ አሁን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የዓለም ንጉሥ መሆኑን እያመለከተን ነው፡፡ ስለዚህ*

*ነገሩ እየቆየ ሲሄድ ክርስቲያኖች "መንግሥተ ሰማያት" የሚለውን በተሳሳተ መንገድ ከመስማት አደጋ ጋር እንጋፈጣለን፡፡ እንደ እውነቱ፣ ኢየሱስ እያለ ያለው፣ እግዚአብሔር ንጉሥ ነው፣ በእኔም በኩል ንጉሥ ሆኖ ተገልጧል ነው፡፡ [ዶ/ር ፒተር ዎከር]*

በማርቆስ ወንጌል 4፥30-31 ማርቆስ ስለ ሰናፍጭ ቅንጣት የፃፈውን ምሳሌ እስኪ አድምጡ፡

*እርሱም አለ፦ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን እናስመስላታለን? ወይስ በምን ምሳሌ እንመስላታለን?*
*እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ናት፥ እርስዋም በምድር በተዘራች ጊዜ በምድር ካለ ዘር ሁሉ ታንሳለች፤ በተዘራችም ጊዜ ትወጣለች ከአትክልትም ሁሉ የምትበልጥ ትሆናለች፥*
(ማር 4፥30-31)

በዚህ ስፍራ ማርቆስ የተለመደውን ሐረግ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚለውን ነው የተጠቀመው፡፡ እስኪ በማቴዎስ 13፥31 የማቴዎስን አፃፃፍ ደግሞ እንመልከት፡

**ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፦ መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤ (ማቴ 13፥31)**

ማቴዎስ ተመሳሳይ የሆነውን ምሳሌ ሲጠቅስ፣ የተጠቀመው ቃል "መንግሥተ ሰማያት" የሚለውን ሲሆን ማርቆስ ግን "የእግዚአብሔር መንግሥት" በማለት ነው፡፡

*ማቴዎስ መንግሥተ ሰማያት በማለት የጠቀሰውን ማርቆስና ሉቃስ ደግሞ ተመሳሳይ የሆነውን ምንባብ የእግዚአብሔር መንግሥት በማለት ጠቅሰውት ካገኛችሁ፣ ሁሉም ተመሳሳይ ነገርን እያመለከቱ መሆኑን የምትመለከቱበት ቁርጥ ያለ መግለጫ ነው ማለት ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መንገድ የማቴዎስን ወንጌል በምታነብቡበት ወቅት አንድ ዐቢይ ሃሳብ የምትመለከቱ ሲሆን እርሱም በሰማይ ያለውን እግዚአብሔር በምድር ከሚኖረው ሰው ጋር የሚያነፃፅር ነው፡፡ እግዚአብሔር መንግሥትን የሚመሠርትበትን መንገድ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ብሎ ሲሰይመው፣ በምድር ላይ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚገዙበትን፣ አመራር የሚሰጡበትን፣ ነገሮችን የሚያከናውኑበትን ደግሞ የዚህ ዓለም መንግሥታት በማለት እንጠራቸዋለን፡፡ ማቴዎስ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲናገር ከዚህ ዓለም ሥርዓት ጋር ያለውን ከፍተኛ ልዩነት የሚያመለክትበት ኃይለኛ መንገዱ ሲሆን፣ በሰማይ ያለው አባታችን ደግሞ የነገሥና የሚገዛ ተመልሶ እንደሚመጣም ተስፋን የሰጠ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ስለዚህ የማቴዎስ ቋንቋ ገናም በምትመጣው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ንግሥናና በዚህ ምድር ያለውን የአገዛዝና የንግሥና ባሕርይ በንፅፅር የሚያሳይ ነው፡፡ ማቴዎስ የሚጠቀምበት "መንግሥተ ሰማያት" የሚለው ቃል ሰማያዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት የምትመጣበትን ጊዜ በተስፋ እንድንጠብቅ፣ እንድናጣጥመውና እንዲሰማን ያደርገናል፡፡ [ዶ/ር ዮናታን ፔኒንግተን]*

አብዛኞቹ ምሁራን እንደሚያምኑት ማቴዎስ ኢየሱስ ለአይሁድ ህዝብ የተናገረበትን መንገድ ጠብቆ ያቆየ ሲሆን፣ ማርቆስና ሌሎቹ የአዲስ ኪዳን ፀሐፍት ደግሞ ሰፋ ባሉት ተደራሲያን ዘንድ ኢየሱስ ሊል የፈለገውን ነገር የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ***"የእግዚአብሔር መንግሥት"*** የሚለውን ሐረግ ተጠቅመዋል፡፡ ይህ እውነት ሆነም አልሆነም፣ ***"መንግሥተ ሰማያት"*** የተሰኘው የማቴዎስ አጠቃቀም ቀደምት ተደራሲያኑ አይሁድ ናቸው ለሚለው አመለካከት ክብደት ይጨምርለታል፡፡

የማቴዎስ ወንጌል አይሁድ ተደራሲያንን ያመላክታል የሚለው ሌላው ገፅታ፣ ማቴዎስ ተደራሲያኑ የአይሁድን ወግ ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆኑን ገምቷል የሚለው ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ብንጠቅስ፣ በማቴዎስ 15፥1-2 ውስጥ ማቴዎስ ይህንን እንዲህ ዘግቦታል፡

> ***በዚያን ጊዜ ጻፎችና ፈሪሳውያን ከኢየሩሳሌም ወደ ኢየሱስ ቀረቡና።***
> ***ደቀ መዛሙርትህ ስለ ምን የሽማግሎችን ወግ ይተላለፋሉ? እንጀራ ሲበሉ እጃቸውን አይታጠቡምና አሉት። (ማቴ 15፥1-2)***

ማርቆስም ይህንኑ ተመሳሳይ ታሪክ በወንጌሉ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 1 እስከ 5 ውስጥ አካትቶታል፡፡ ማርቆስ ግን ሮማውያን ተደራሲያኑ ወጉን በሚገባ እንዲረዱለት በማሰብ ስለ አይሁድ የእጅ መታጠብ ወግ ሦስት ተጨማሪ ጥቅሶችን ለማብራሪያነት ተጠቅሟል፡፡ ማቴዎስ ለእርሱ ተደራሲያን ያንን የመሰለ ማብራሪያ እንደማያስፈልገው ተሰምቶታል፡፡

ማቴዎስ ለአይሁድ ተደራሲያን እንደፃፈ እንያዝና፣ በወንጌሉ ባህርይ ውስጥ ያለ ስፍራው የገባ የሚመስል አንድ ነገር እንመለከታለን፡፡ በጣም በጥቂት ስፍራዎች፣ ማቴዎስ ኢየሱስ በአራማይስጥ የተናገራቸውን ይጠቅስና እነዚያንም የአራማይስጥ ቃላት በተደራሲያኑ ቋንቋ ተርጉሟል፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 27፥46 የተነገረውን አድምጡ፡

> ***ኢየሱስ፦ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው። (ማቴ 27፥46)***

ቀደምት ተደራሲያኑ አይሁድ መሆናቸውን እያወቀ እንኳ፣ ማቴዎስ ለምን በዚህ መንገድ ጻፈ ለሚለው ሃሳብ የሚሰጡ የተለያዩ ማብራሪያዎች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ ምንም እንኳን ቀደምት ተደራሲያኑ አይሁድ ቢሆኑም፣ ሁሉም አይሁድ ብቻ አልነበሩም፡፡ ስለዚህ፣ አይሁዳውያን ያልሆኑትንም አንባቢያኑን ለማካተት እነዚህን ማብራሪያዎች ጨምሮ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛ፣ ከማቴዎስ ተደራሲያን ውስጥ የአራማይስጥ ቋንቋ የማያውቁና ከፓለስታይን ውጪ ባሉ ምድሮች የሚኖሩ ህዝቦች ሊኖሩባቸውም ይችሉ ይሆናል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ምናልባትም ማቴዎስ መረጃውን ከሌላ ምንጭ ቀድቶት ሊሆንም ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 27 ቁጥር 46 ውስጥ የምናገኘው ፍቺ፣ በማርቆስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 34 ውስጥም ይገኛል፣ ምናልባትም ማቴዎስ ያንን እንደ ምንጭ ተጠቅሞበት ይሆናል፡፡

በሁሉም ወቅቶች፣ መረጃዎቹ ሁሉ ማቴዎስ ወንጌሉን በተቀዳሚነት ለአይሁድ ክርስቲያኖች ጽፏል፣ ይህንንም ያደረገው ለእነርሱ አስፈላጊ የሆኑትን በማንሳት በኢየሱስ ያላቸውን እምነት ለማጠንከር ነው የሚለውን ሃሳብ ያጠናክሩታል፡፡

የመጀመሪያውን ወንጌል ጸሐፊና ተደራሲያን ከመረመርን፣ አሁን ደግሞ የተጠናቀረበትን ወቅት እንመረምራለን፡፡

# ወቅት

አንድ መጽሐፍ ስለተጠናቀረበት **"ወቅት"** ስንናገር፣ ከታሪካዊ አውዱ ጋር የሚዛመዱ በርካታ ነገሮች ወደ ልቡናችን ይመጣሉ፡፡ እነርሱም፡- የተጠናቀረበት ቀን፣ የተጠናቀረበት ስፍራ፣ የተደራሲያኑ አድራሻ፣ የተጻፈበት ዓላማ ናቸው፡፡ መጽሐፉ መቼ፣ የት፣ ለማን፣ እና ለምን እንደተጻፈ ማወቃችን፣ ስለ አውዱ በርካታ መረጃዎችን ይሰጠናል፡፡ ታሪካዊ መቼቱን፣ ሰዋሰዉንና ስነ ቃሉን፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ እሳቤዎችን እና የንግግር ቃናዎቹን እንድንረዳ ያግዘናል፡፡ በምላሹም፣ ይህ መረጃ መጽሐፉን እንድንረዳና እንድናዛምደው ያግዘናል፡፡

የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበትን ወቅት ሦስት ገፅታዎች እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የተፃፈበትን ቀን፤ ሁለተኛ፣ የጸሐፊውንና የተደራሲያኑን አድራሻ እና ሦስተኛ፣ ማቴዎስ የጻፈበትን ዓላማ እንመለከታለን፡፡ አሁን የማቴዎስ ወንጌል በተጻፈበት ቀን እንጀምር፡፡

## ቀን

በመጀመሪያ፣ አብዛኞቹ ምሁራን እንደሚያምኑት፣ ማቴዎስ ምናልባት የማርቆስን ወንጌል ከምንጮቹ አንዱ አድርጎ ተጠቅሞ ይሆናል፡፡ ወደ ኋላ በምንመለከታቸው ትምህርቶች እንደምናየው፣ ማርቆስ የተጻፈው በ64 ዓ.ም. አካባቢ ነው፡፡ ይህ ትክክል ከሆነ፣ ማቴዎስ የተጻፈበት ጊዜ ሊሆን የሚችለው በ60 ዎቹ አጋማሽ ላይ ነው ማለት ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ማቴዎስ የኢየሱስ ሐዋርያ ነበር፡፡ ይህም ማለት ወደ 30 ዓ.ም. አካባቢ ከኢየሱስ ጋር ወደ አገልግሎት ሲገባ፣ አዋቂ ሰው ነበር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ፣ ማቴዎስ ያልተለመደ ረጅም ዕድሜ ካልኖረው በስተቀር፣ ቢዘገይ ቢዘገይ ሊጽፍ የሚችልበት ወቅት በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት ማብቂያ ላይ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይህ እንግዲህ ማቴዎስ ጽፎበታል የተባለውን ሚዛናዊ የሆነ ሰፊ ጊዜን ይሰጠናል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ሰፊ ክልል ውስጥ ሆነን በማቴዎስ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ዝርዝሮችን በመመልከት ሊሆኑ የሚችሉ ቀናትን ማስቀመጥ እንችላለን፡፡ በተለይም፣ ማቴዎስ ደጋግሞ መቅደሱን፣ ሰዱቃውያንን ማለትም ከመቅደሱ ጋር ቅርበት ያላቸውን ይጠቅሳል፡፡ ጥቂቶቹ ማስረጃዎች በአብዛኛው ታሪካዊ ሲሆኑ፣ ጥቂቶቹ ግን ማቴዎስ እስከ ጻፈበት ዘመን ድረስ መቅደሱም ሆነ ሰዱቃውያኑ ወሳኝ እንደ ነበሩ ያመለክታሉ፡፡ መቅደሱ በ1970 ዓ.ም የተደመሰሰ ከሆነ፣ ማቴዎስ ደግሞ ከዚያ ቀድሞ ከጻፈ ማስረጃዎቹ የበለጠ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

በነዚህ ሁሉ መረጃዎች ታግዘን፣ ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው በ60ቹ ማብቂያ፣ እንዲያውም በ67 ወይም በ68 ውስጥ ብሎ መደምደም ተመራጭ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ እንደ እድል ሆኖ፣ ማቴዎስ መቼ ጻፈው የሚለውን ጊዜ ግምት ማወቁ ጠቃሚ ቢሆንም፣ ወንጌሉ የተጻፈበትን ትክክለኛ ቀን የማወቁ ጉዳይ አስተምህሮውን ከመተርጎም አንጻር አጠያያቂነቱ እምብዛም ነው፡፡

ወንጌሉ የተጻፈበትን ወቅት ከተመለከትን፣ የጸሐፊውን እና የተደራሲያኑን መልክዓ-ምድራዊ አድራሻ እንመልከት፡፡

## አድራሻ

ምሁራኑ ይህ ወንጌል በተጻፈበት ስፍራ አንጻር ምንም ክርክር ያላደረጉበት መሆኑን በማንሳት መጀመራችን ተገቢ ነው፣ ስለዚህ ድምዳሜያችን ግትር ሊሆን አይገባውም፡፡ ሆኖም፣ እርባና የሌላቸው ዝርዝሮችም እንዳሉ አንርሳ፡፡

ለመጀመር ያህል፣ በተቀዳሚነት ማቴዎስ የጻፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች በመሆኑ ምክንያት፣ ወንጌሉን ያቀረበው በርካታ አይሁዳውያን በሚኖሩበት አካባቢ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አይሁድ በትውፊት እንደሚኖሩበት የሚነገርለት ከመሆኑ እና በዚያም አካባቢ በብዛት ስለሰፈሩ ፓለስታይን አንዱ ገሃድ አማራጭ ነው፡፡

ሆኖም የሶሪያ አንዱ ክፍል ደግሞ ቀላል ነው የማይባሉ አይሁድ የሚኖሩበት ነው፡፡ የሶሪያዋ አንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ የሆነው ኢግናቲየስ፣ ከማቴዎስ ወንጌል ጋር ቅርበት አላቸው ከሚባሉ የቤተክርስቲያን አባቶች ቀደምት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በርካታ ምሁራን ማቴዎስ የጻፈው በሶሪያዋ አንጾኪያ ለሚኖሩ አማኞች ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡

እርግጥም፣ ማቴዎስ በልቡናው ሰፋ ያሉ ተደራሲያን ነበሩት የሚለውን ሊሆን አይችልም ብለን አንበይንም፣ ይልቁኑም በሜዲትራኒያን አካባቢ ላሉ የአይሁድ ክርስቲኖች በጥቅሉ እንደጻፈ እንረዳለን፡፡

ፓለስታይን፣ ሶሪያ ወይም አይሁድ በበርካታ ቁጥር የሚኖሩበት እና በሮሜ ግዛት ውስጥ የነበረ ስፍራ በጠንካራ አይሁዳዊ ባህርይ ለተገነባው የማቴዎስ ወንጌል አድራሻነት ሊገጥም ይችላል፡፡

> ***በመጀመሪያው ምዓተ ዓመት አካባቢ፣ የአይሁድ ህዝብ በሮም ግዛት አብዛኛ ስፍራዎች፣ እንዲያውም በሩቅ ምሥራቅም ጭምር ተበታትነው ነበር፡፡ ይህም ወደ ኋላ ረጅም ዘመናትን ይጓዛል፡፡ ከባቢሎን ምርኮ ዘመን አንስቶ አይሁዳውያን ከፓለስታይን ምድር ወጪ ይኖሩ ነበር፡፡ ስለዚህም እስከ ሩቅ ምሥራቅም ድረስ በመዝለቅ ይኖሩ ነበር፡፡ ይህም በሜሶፖታሚያ፣ በዘመኗ ኢራቅ ውስጥም ማለት ነው፡፡ ከዚያም ወደ ሶሪያ፣ ደማስቆ እና በዲያስፖራው፣ ዲያስፖራ የሚለው ቃል የአይሁድን መበተን የሚገልፅ ቃል ነው፡፡ ከዚያም፣ በምዕራብ እስከ ትንሿ እስያ፣ የዛሬዋ ቱርክ እና አይሁድ በብዛት እስከሚኖሩበት በሮም እስከሚገኘው የቲቤር ወንዝ ድረስ ሰሜን አፍሪካን ሳንዘነጋ ተበትነው ነበር፡፡ የቀሬናው ስምዖን የተሰኘው ሰው ከሰሜን አፍሪካ ወደ ኢየሩሳሌም እንደመጣ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ***

*እናነባለን፡፡ ስለዚህ፣ አይሁድ ይኖሩበት የነበረውን የሮሜን ግዛት ምሥራቃዊ ኢጋማሽና ሩቅ ምሥራቅን ጨምሮ መገመት እንችላለን፡፡ [ዶ/ር ፒተር ዎከር]*

የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈበትን ወቅትና ስፍራ አስመልክቶ ተነጋግረናል፣ አሁን ደግሞ ማቴዎስ ወንጌሉን ሲጽፍ ዓላማ ያደረገውን እንመለከታለን፡፡

## ዓላማ

ሰፋ ባለ ሁኔታ ስንናገር፣ ማቴዎስ የጻፈበት ምክንያት የኢየሱስ ማንነትና ያደረገው ነገር እጅግ ወሳኝ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም ግን፣ ከዚያም የጠበበና የቅርብ ግብም ነበረው፡፡ በተለይም፣ ማቴዎስ የጻፈው የአይሁድ ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሃዊ ንጉሣቸው መሆኑን በማወቅ በእምነታቸው እንዲበረቱ ነው፡፡

ማቴዎስ በጻፈበት ወቅት፣ ወደ ክርስትና የመጡ አይሁዳዊያን በአይሁድ ባለሥልጣናት፣ በቀድሞ ጓደኞቻቸውና በቤተሰብ አባሎቻቸው በብርቱ ተቃውሞ ይደርስባቸዋል፡፡ በዚያን ዘመኑ የሜድትራኒያኑ ዓለም ውስጥ፣ ስደት ለአይሁድ ክርስቲያኖች አንደኛው የሕይወት ዘይቤአቸው እንደ ነበር የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በግልፅ ያስቀምጥልናል፡፡

የሐዋርያት ሥራ 8፥1 እንዲህ ይነበባል፡

*በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ። (ሐሥ 8፥1)*

ከስደቱም የተነሳ፣ ኢየሱስን እንደ መሲሃቸው ይከተሉ የነበሩ አይሁድ ክርስትናን በመተው ወደ ቀደመው እምነታቸው የመመለስ ፈተና ይገጥማቸው ነበር፡፡ ለዚህ ፈተና ምላሽ ይሆንም ዘንድ፣ ማቴዎስ ኢየሱስ እርሱ እውነተኛው መሲህና መንግሥተ ሰማያትን ያመጣ መሆኑን ለማሳሰብ ጻፈላቸው፡፡ ወንጌሉ የማበረታቻና የማጽናኛ ታሪክ ነው፡፡ ሆኖም ግን ኢየሱስ መንግሥቱን ያመጣው ብዙዎቹ በሚጠብቁት መንገድ አለመሆኑና መንግሥቱ የሚጠይቀው ነገር ትልቅ መሆኑ ደግሞ ተግዳሮት ነው፡፡

በዚህ አውድ፣ ኢየሱስ ብሉይ ኪዳን ከመሲሃዊ መንግሥት የሚጠብቀውን ሊያሟላ መጀመሩን ማቴዎስ ለተደራሲያኑ ያረጋግጥላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ፣ መንግሥተ ሰማያት ግን ገና ወደ ሙላት አልመጣችም፡፡ ስለዚህ፣ ማቴዎስ የጻፈው አይሁድ አማኞች ንጉሡ ተመልሶ መጥቶ ነገሮችን እስኪያስተካክል፣ ኢየሱስ የመንግሥቱን ጠላቶች እስኪያጠፉ እና ታማኝ ህዝቦቹን ወደ መንግሥቱ ምሉዕ በረከት እስኪያስገባ ድረስ በታማኝነት እንዲዘልቁ ለማበረታታትም ነው፡፡

መንግሥተ ሰማያት የሚለውን መሪ ቃል ማቴዎስ ደጋግሞ የሚያነሳው ለዚህ ነው፡፡ እንዲያውም፣ **"ንጉሥ" እና "መንግሥት"** የሚሉትን ቃላት በወንጌሉ ውስጥ ከ75 ጊዜያት በላይ ተጠቅሟል፡፡ ሌሎቹ ሦስት የወንጌላት ፀሐፍት በአንድ ላይ የተጠቀሙባቸው ከ110 ጊዜያት ባነሰ ነው፡፡ ለማቴዎስ፣ አይሁድ ተደራሲያኑን ለመሞገት እና ለማበረታታት ተመራጩ መንገድ ለመሲሁ ንጉሣቸውና ስለ መንግሥቱ መንገር ነበር፡፡

**በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ለመንግሥተ ሰማያት ትልቅ አፅንዖት ተሰጥቶ እናገኛለን፡፡ ማቴዎስ ወንጌሉን የሚጀምረው ኢየሱስ እውነተኛው ግንድ፣ ከዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ እንደ ሆነ ማሳየትን ዒላማ አድርጎ የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ በመጥቀስ ነው፡፡ ይህ ከዳዊት ዘር የሆነው ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፡፡ ተደራሲያኑ፣ ቀደምት ተደራሲያኑ፣ አይሁድ ናቸው፡፡ ይህም መጽሐፍ ለህዝቡ የሚናገረው "እውነተኛው ንጉሣችሁ እነሆ" ብሎ እንደሆነ እናምናለን፡፡ እርሱም መንግሥተ ሰማያትን በተጨበጠ መገለጫዋ ማለትም በወንጌሉ ውስጥ "መንግሥተ ሰማያት" የሚለውን ቃል ሲጠቀም የክርስቶስ አገዛዝ በሁሉም ህዝብና በሁሉም እርከን ላይ የሚሠራ መሆኑን በአፅንዖት ይገልፃል፡፡ ጥያቄው የሥልጣን ጉዳይ ነው፡፡ ፈሪሳውንና ሰዱቃውያን ኢየሱስን አዘውትረው የሚጠይቁት "እነዚህን የምታደርገው በምን ሥልጣን ነው?" እያሉ ነበር፡፡ ወንጌሉ የሚደመደመው "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል" በሚለው የኢየሱስ ቃላት ነው፡፡ ይህ የመንግሥት ሃሳብ ከብሔርተኝነት የዘለለና ሰዎች ሁሉ ሊጠብቁት የሚገባ ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ ነው፡፡ ክርስቶስ እያንዳንዷቷን የፍጥረት ክፍል ሁሉ የሚገዛ ንጉሥ መሆኑን የገለጠበት ዐረፍተ ነገር ይህ ነው፡፡ [ቄስ ጂም ማፐልስ]**

የማቴዎስን ወንጌል ዳራ ካጠናን፣ አሁን ደግሞ ወደ ወንጌሉ ውቅርና ይዘት መለስ እንላለን፡፡

# ውቅርና ይዘት

የማቴዎስን ወንጌል ጥቂት የአወቃቀር ገፅታዎች አስመልክቶ ልብ ልንለው የሚገባ ስምምነት በምሁራኑ መካከል አለ፡፡ የዚህ ስምምነት ምክንያቱ ማቴዎስ እጅግ ጠቃሚ ቁልፍ የሚሰጠን የመሆኑ እውነታ ነው፡፡ በወንጌሉ ውስጥ ዐቢይ ሽግግር መኖሩን ለማሳየት በአምስት የተለያዩ ወቅቶች፣ "ኢየሱስም ይህንን ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ ..." የሚለውን ሐረግ ይጠቀማል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህን የመሰለው ዐረፍተ-ነገር በክፍልፋዩ ማብቂያ ላይ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ በአዲሱ ክፍልፋይ የመጀመሪያ ዐረፍተ-ነገር ሆኖ ይታያል፡፡ ሁልጊዜ ሚያመለክተው ግን ዐቢይ ሽግግር መኖሩን ነው፡፡

እነዚህን የአወቃቀር ምልክቶች ተከትሎም፣ የማቴዎስ ወንጌል በሰባት ክፍሎች እንደሚከፈል አብዛኞቹ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ በማቴዎስ 7፥28፣ 11፥1፣ 13፥53፣ 19፥1 እና 26፥1 አምስት በመሸጋገሪያ ዐረፍተ-ነገሮች የተዋቀሩ ክፍሎች አሉ፡፡ ከዚያም ማቴዎስ የመግቢያና የመደምደሚያ ታሪክ አስገብቶበታል፡፡

- ወንጌሉ የሚጀምረው ኢየሱስን እንደ መሲሃዊ ንጉሥ በሚገልጠው በማቴዎስ 1፥1 - 2፥23 በተመዘገበው የመግቢያ ትረካ ነው፡፡
- የመጀመሪያው ዐቢይ አንጓ የመንግሥቱን ወንጌል የሚገልጠው በማቴዎስ 3፥1 - 7፥29 ያለው ነው፡፡

- ሁለተኛው ዐቢይ አንጓ በመንግሥቱ መስፋፋት ላይ የሚያተኩረውና በማቴዎስ 8፥1-11፥1 የሚገኘው ነው፡፡

- ሦስተኛው ዐቢይ አንጓ የመንግሥቱን ምልክቶችና ምሳሌዎች የሚገልጸው በማቴዎስ 11፥2-13፥53 የሚገኘው ነው፡፡

- አራተኛው ዐቢይ አንጓ በእምነትና በትልቅነት ላይ የሚያተኩረው በማቴዎስ 13፥54 ጀምሮ እስከ 18፥35 የሚዘልቀው ነው፡፡

- አምስተኛውና የመጨረሻው ዐቢይ አንጓ ስለ መንግሥቱ የአሁን መገፋትና ወደፊት ስለሚኖረው ድል የሚናገረው በማቴዎስ 19፥1 - 25፥46 የሚዘልቀው ነው፡፡

- በመጨረሻም፣ የንጉሡን ሞትና ትንሣኤ የሚተርከው በማቴዎስ 26፥1-28፥20 የሚገኘው መደምደሚያ ነው፡፡

እነዚህ የማቴዎስ ወንጌል ክፍልፋዮች የኢየሱስን ታሪክ ዕድገት የሚያሳዩ ሲሆን፣ ያም መንግሥተ ሰማያትን በምድር ያመጣ መሲሃዊ ንጉሥ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

በማቴዎስ 1፥1-2፥23 በተገለጠው መግቢያ በመጀመር እያንዳንዳቸውን በጥልቀት እንመልከታቸው፡፡

# መግቢያ፡ መሲሃዊ ንጉሥ

የማቴዎስ ወንጌል መግቢያ ኢየሱስን እንደመሲሃዊ ንጉሥ የሚያስተዋውቀን ሲሆን በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡ የትውልድ ሃረግና የልጅነት ታሪክ፡፡

## የትውልድ ሃረግ

የትውልድ ሃረጉ በማቴዎስ 1፥1-17 ውስጥ ይገኛል፡፡ በቴክኒካዊ ቋንቋ ስናስቀምጠው፣ የመጀመሪያው ጥቅስ መግቢያ ወይም ርዕስ ሲሆን በዚያም ኢየሱስ የእስራኤል መሲሃዊ ንጉሥ መሆኑን ማቴዎስ ጠቅለል አድርጎ አቅርቦበታል፡፡

ማቴዎስ 1፥1 እንዲህ ይነበባል፡

***የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ። (ማቴ 1፥1)***

ገና ከጅማሬው፣ ማቴዎስ በእስራኤሉ ንጉሥ በዳዊት ላይ እና በአይሁድ ህዝብ አባት በአብርሃም ላይ ልዩ አጽንዖት ሰጥቷል፡፡

ከዚህ መግቢያ በመቀጠል፣ የትውልድ ሃረጉ ራሱ በቁጥር 2 ይጀምራል፡፡ በማቴዎስ 1፥17 መሠረት፣ የትውልድ ሃረጉ በሦስት አንጓዎች እያንዳንዳቸው ዐሥራ አራት ትውልዶችን ይዘው የተዋቀረ ነው፡፡ የመጀመሪያው ከዘሩ የሚወጣው ዓለምን እንደሚገዛ ተስፋ በሰጠበት፣ በአብርሃም ቃል ኪዳን ይጀምራል፡፡

ሁለተኛው አንጓ ደግሞ የዳዊትን ስርወ-መንግሥት ለዘላለም በማፅናት የአብርሃምን ቃል ኪዳን እንደሚፈፅም ተስፋን በመስጠበት በንጉሥ ዳዊት ይጀምራል፡፡ ሁለተኛው አንጓ የሚደመደመው የእግዚአብሔር ህዝብ በኃጢአታቸውና ቃል ኪዳኑን ባለመጠበቃቸው ምክንያት ከተስፋዪቱ ምድር እንደሚሰደዱ በመናገር ነው፡፡

የትውልድ ሃረጉ ሦስተኛ አንጓ ከስደት እስከ ኢየሱስ ዘመን ድረስ ይዘልቃል፡፡ እስራኤል የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አፈረሰች በቃል ኪዳኑ እርግማንም ስር ወደቀች፡፡ እግዚአብሔር ግን አሁንም ከአብርሃምና ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በመፈፀም እስራኤልን መባረክ ዓላማ ነበረው፡፡ ያለፉት ነገሥታት ሁሉም በደሉ፡፡ የመጨረሻው የእስራኤል ንጉሥ፣ የእስራኤልን ሥርወ- መንግሥት የሚያፀናው ግን፣ በመጨረሻው መጣ፡፡

የኢየሱስ ዝርያዎች ዝርዝር የሚያበቃው እንዲህ በሚነበበው፣ በማቴዎስ 1፥16 ነው፡

***ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ። (ማቴ 1፥16)***

በዚህ መንገድ፣ ኢየሱስ በዮሴፍ አማካይነት የዳዊት ዙፋን በትክክል የተገባው መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

> *መሲሁ ከዳዊት ዘር ሊሆን የሚገባው አስቀድሞ በተነገረው ትንቢታዊ መገለጥ መሠረት ነው፡፡ ይህም ወደ ኋላ ወደ ይሁዳ ነገድ ይሄድና በዘፍጥረት ውስጥ ከዘሩ ንግሥና እንደሚመጣ የተነገረውን ትንቢት ያመለክታል፡፡ በእርግጥ ትንቢቱ የተፈፀመው፣ በዳዊት፣ በታላቁ በእስራኤል ንጉሥ በንጉሥ ዳዊት ነው፡፡ ከዳዊት ቀጥለው የመጡት ነገሥታት ሁሉ በበጎም ሆነ በክፉ የሚነፃፀሩት ከእርሱ ጋር ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ ከዚያ በኋላ፣ ከዳዊት ከራሱም ጋር ቃል ኪዳን ተገብቷል፡፡ ዳዊት ለነቢዩ ናታን፣ ለእግዚአብሔር ቤትን፣ መቅደስን ለመሥራት ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ናታን ወደ እርሱ መጥቶ **"አንተ ቤትን ለእግዚአብሔር አትሠራም፤ እርሱ ግን የታመነ ቤትን ይሠራልሃል"** ነበር ያለው፡፡ ቤት ሲልም ሥርወ-መንግሥት ማለት ነው፡፡ ይህም በ1ኛ ሳሙኤል 7 ያለው ሲሆን፣ እግዚአብሔር ቤትን እንደሚሠራለት የተነገረው ትንቢት፣ መንግሥቱን ለዘላለም ያፀናል፣ ዘሩም በዳዊት ዙፋን ለዘላለም ይነግሣል፣ በማለት ተከትለው ለሚመጡት መሲሃዊ ትንቢቶች መሠረት ሆነ፡፡ እናም ነቢያት፣ ከውድቀት በኋላ ወደ ኋላ ሲያመለክቱ፣ በተለይም የዳዊትን ዝርያ አስመልክቶ፣ ያመለክቱ የነበረው እግዚአብሔር የዳዊትን መንግሥት እግዚአብሔር ወደ ቀደመው ክብሩ እንደሚመልስ፣ ይህም የሚፈፀመው ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥን በማስነሳት እንደሆነ ነበር፡፡ እናም ንጉሡ፣ መሲሁ፣ የሚመጣው ከዳዊት ዘር ነው፡፡ [ዶ/ር ማርክ ስትራውስ]*

ከኢየሱስ የትውልድ ሃረግ የሚከተለው፣ የልጅነት ታሪኩ ነው።

## የልጅነት ታሪክ

የኢየሱስ የልጅነት ታሪክ ከማቴዎስ 1፥18-2፥23 ይዘልቃል። ይህ ክፍል፣ በሉቃ ስወንጌል ከሚገኘው 116 ጥቅሶች ካሉት ጋር ሲነፃፀር፣ አጭርና 31 ጥቅሶች ብቻ ያሉት ነው። በዚህ ክፍል፣ የማቴዎስ ዓላማ ውሱን ነበር። እያንዳንዱ አምስት አጫጭር አንቀፅ ትኩረትን ወደ አንድ ማዕከላዊ እውነታ ማለትም መሲሁ ኢየሱስ ተወለደ ወደሚለው መሳብ ነበር። እያንዳንዱ አንቀፅ ስለ አንድ ታሪክ ያነሳና ታሪኩ የብሉይ ኪዳንን የመሲሁን ጥበቃ እንዴት እንዳሟላ ያብራራል።

ከኢየሱስ የልጅነት ታሪክ ከምንማራቸው አስደሳች ታሪኮች አንዱ፣ እርሱ ሰብዓዊ አባት እንደሌለው የሚናገረው ነው። በፋንታው ግን በቀጥታ፣ እግዚአብሔር አባቱ ነበር። ማርያም ገና ድንግል ሳለች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ፀነሰች።

በኢየሱስ የትውልድ ሃረግ ውስጥ ይህ ነገር ደካማ ነገር ነው፣ የሚል ነቀፋ በክርስትና ላይ ያስነሳል። ያም፣ እርሱ የዳዊት የሥጋ ዘር እስካልሆነ ድረስ፣ የዳዊትን ዙፋን ይገባኛል ሊል አይችልም የሚለው ነው። ሆኖም ግን በ1ኛ ዜና 1-9 ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትውልድ ሃረጎች ስንመለከት፣ የጉዲፈቻ ወላጅነትን በዘር ውስጥ ደጋግመው ሲያካትቱ እናገኛለን።

ከዚህም በተጨማሪ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፣ መለኮትም ነው። ያም ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በምልዓት ይፈፅማል ማለት ነው። ሰብዓዊ ብቻ የነበሩት ነገሥታት ግን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በምልዓት ፈፅመው አያውቁም። እናም፣ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዳዊት የገባውን ምሉዕ የቃል ኪዳን በረከት ሊወርሱ አይችሉም። ስለዚህም እግዚአብሔር፣ ቃል ኪዳኑ ይጠበቅና የቃል ኪዳኑም የበረከት ተስፋ ይፈፀም ዘንድ ፍፁም የሆነውን ልጁን ንጉሥ አድርጎ መላክ ነበረበት።

> ***መሲሁ እንደ ሰው ከዳዊት ዘር እንደሚመጣ ግልጽ ነው። በዚህም በርካታ አስፈላጊ እውነቶች አሉ። ከዚህም በተጨማሪ መሲሁ አምላክ ደግሞም መለኮትም ሊሆን የተገባው መሆኑን መረዳትም ወሳኝ ነው። ግን ለምን እንዲያ ሆነ? በዋናነት እኛ እንደ ሰብዓዊ ሰዎች ችግራችን በእርሱ ላይ ኃጢአትን ያደረግን መሆናችን ነው። እርሱ መልሱን ማስገኘት ነበረበት። መፍትሄውን ሊያመጣ ግድ ነው። ኃጢአታችን በእግዚአብሔር ፊት እንዳላየ የሚያልፈው ስላልሆነ ይቅርታ ማግኘት ግድ ነበር። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር ጻድቅና ፍትሃዊ ነው። ስለዚህ፣ "ጥጌን ይጌ እንዳላየ አልፋለሁ" ወይንም "የቻላችሁትን ሁሉ አድርጉ" ሊል አይችልምና ኃጢአታችንን እንዳላየ እንዲያልፈው መጠበቅ የለብንም። ያን ካደረገ ራሱን መካዱ ነው። እንግዲያው፣ ይቅር ይለን ዘንድ፣ እርምጃ ሊወስድ ይገባዋል። የራሱን የጽድቅ ጥያቄው አሟልቶ ይረካ ዘንድ፣ መፍትሄውን ማምጣት ይገባዋል። እግዚአብሔር ራሱ ሊፈፅመው ይገባል። ብሉይ ኪዳንን በምታነቡበት ወቅት፣ ደግሞ ደጋግሞ ጉዳዩ ሲነሳ ታገኙታላችሁ። ለምሳሌ፣ ዮናስ 2፥9 "ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው" የሚለውን ልታስቡ ትችላላችሁ። ያም ማለት***

*እግዚአብሔር ራሱ የሚያዘጋጀው ነው ማለት ነው፡፡ መፍትሄውን የሚያመጣው እግዚአብሔር ነው፡፡ ይቅር ማለት ያለበት እግዚአብሔር ነው፡፡ እናም ድነት በመሲሁ በኩል የሚመጣ ከሆነ፣ እኛን ወክሎ ሰው ሊሆን ይገባዋል፡፡ ደግሞ ጌታም ሊሆን ይገባዋል፡፡ የሚያድን ጌታ ማለት ነው፡፡ የራሱን ቅድስናና ጽድቅ የሚያረካ ጌታ፣ እናም መሲሁ መለኮት ሊሆን ይገባዋል፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

ማቴዎስ በወንጌሉ መግቢያ ላይ፣ ኢየሱስን የዳዊት ንጉሣዊ ልጅ ለአብርሃምና ለእስራኤል ሁሉ የእግዚአብሔርን በረከት እንደ ተቀበለ መሲሃዊ ንጉሥ አቅርቦታል፡፡ በዚህም መንገድ፣ ማቴዎስ ጠቅላላው መጽሐፉ ላነገበው ርዕሰ ጉዳይ ለምሥራቹ ወንጌል መደላድል አስቀምጧል፡፡

መግቢያውንም ተከትሎ የወንጌሉ አምስት ስነ-ጽሑፋዊ ክፍልፋዮች ይመጣሉ፡፡ አምስቱም አንጓዎች በሁለት ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም ማቴዎስ የኢየሱስን ማንነት የገለጠበት ትረካና ኢየሱስ የተናገረውን የዘገበበት የንግግር ክፍሎች ናቸው፡፡

# የመንግሥቱ ወንጌል

የማቴዎስ ወንጌል የመጀመሪያው አንጓ ስለ መንግሥተ ሰማያት ወንጌል ይተርክልናል፡፡ ይህ ክፍል ከማቴዎስ 3፥1 እስከ 7፥29 ይዘልቃል፡፡

## መሲሁ መጥቷል

የትረካው አንጓ በማቴዎስ 3፥1 ይጀምርና በ4፥25 ያበቃል፡፡ በዚህ ስፍራ፣ ማቴዎስ መሲሁ ንጉሥ መጥቷል፣ መንግስተ ሰማያትንም ወደ ምድር አምጥቷል በማለት አውጇል፡፡

የትረካው የመጀመሪያ ክፍል ማቴዎስ 3፥1-12 ሲሆን፣ በዚያም መሲሁ በቶሎ እንደሚመጣና የታመኑትንም ህዝቡን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ መጥምቁ ዮሐንስ አውጇል፡፡ ከእርሱ በራቁ ሕዝቡ ምክንያት እግዚአብሔር ፍርድን ስለጣለባቸው መንፈስ ቅዱስ ለ400 ዓመታት ያህል በእስራኤል ውስጥ በአንፃራዊነት የማይሠራበት ጊዜ ነበር፡፡ አሁን ግን፣ የብሉይ ኪዳን ነቢያት እንደተናገሩት፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲፈስስ አዲስ ቀን ሊመጣ ቀርቦ ነበር፡፡

ትረካው በማቴዎስ 3፥13-17 በኢየሱስ መጠመቅ ይቀጥላል፡፡ በዚህ ሁነት ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ወረደ፣ ለመሲሀዊ አገልግሎቱም ቀባው፣ አብም ከሰማት፣ **"ይህ ልጄ ነው"** በማለት በመዝሙር 2፥7 የተሰጠውን ንጉሣዊ ማዕረግ ከኢየሱስ ጋር አዛመደው፡፡

መለኮታዊው ድምፅ በተጨማሪም በኢሳያስ 42፥1-2 መከራ የሚቀበለውን አገልጋይ **"በእርሱ ደስ የሚለኝ፣ የምወድደው"** በማለት ኢየሱስን ሲገልፀው አውጅታል፡፡ ኢየሱስ ንጉሣዊ መሲህ ነው፣ ግን የተለየ ንጉሥ ነበር፡፡ ጥሪውን የሚፈፅመው በመከራ ነበር፡፡

በማቴዎስ 4፥1-11 በሚገኘው፣ በትረካው ቀጣይ ታሪክ ውስጥ፣ ኢየሱስ የተቀበለውን ይህንን ንጉሣዊ መከራን የሚቀበል መሲህ ሰይጣን ሲገዳደረው እናገኛለን፡፡ ለሦስት ጊዜያትም ኢየሱስ

መከራ የማይነካው መሲህ ይሆን ዘንድ **“እንደ ሰው አትራብ፣ ያለምንም ስቃይ እንዲያምኑህ በማድረግ ሰዎችን አስደንቅ፡፡ መንግሥታትንም ምንም ስቃይ ሳያገኝህ ግዛ”** በማለት ፈትኖታል፡፡ ኢየሱስ ግን የእርሱን መከራ የሚቀበል መሲሃዊነት ባህርያት የሚከዱትን ቀላል መሳይ መንገዶች ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡

ከዚያም በማቴዎስ 4፥12-17፣ ኢየሱስነየመንግሥቱን ወንጌል በመስበክ የአደባባይ መሲሃዊ አገልግሎቱን ጀመረ፡፡

ማቴዎስ በ4፥17 ውስጥ የኢሱስን መልእክት እንዴት ጠቅለል አድርጎ እንዳቀረበው አድምጡ፡

> *ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፡- መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ኢያለ ይሰብክ ጀመር። (ማቴ 4፥17)*

እንደ ማቴዎስ አጻጻፍ፣ ኢየሱስ የሰበከው መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች በማለት መሆኑን ገልጧል፡፡ ይህም በእርሱ አገልግሎት፣ መንግሥተ ሰማያትን ወደ ምድር እንደሚያመጣ ያመለክታል፡፡ ይህም መንግሥት ኃጢአተኛነታቸውን በመናዘዝ በታማኝነት ኢየሱስን እንደ ንጉሥ ለሚከተሉ ሁሉ ነው፡፡

> *“**መንግሥተ ሰማያት**” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ሲሆን፣ እንደማሰበውም “**የእግዚአብሔር መንግሥት**” ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በመካከላቸው ልዩነት የለም ከሚሉት ከአብዛኞቹ ምሁራን ጋር እስማማለሁ፡፡ እውነታውም ኢየሱስ ራሱ በቅርብ መሆኑ ስለተገለጠ ወይም አንዳንድ ትርጉሞች እንዳስቀመጡትም በደጅ በመሆኑ፣ የእግዚአብሔር አገዛዝ በኢየሱስ ስብዕናና ሥራ የመጣ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ሆኖም ግን ምልዓቱ ገና የሚመጣ መሆኑንም ያሳያል፡፡ “**ምልዓት**” የሚለው ቴክኒካዊ ቃል፣ በክርስቶስ ዳግም ምፅዓት የሚፈጸመውን ሲያመለክት፣ ከዚህም የተነሳ ክርስቲያኖች ሊኖሩ የሚገባቸው በዚያ አስተሳሰብና እሴት መሠረት ይሆናል ማለት ነው፡፡ በአንድ እግራቸው የመጨረሻውን ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት በእምነት በመርገጥ፣ በሌላኛው እግራቸው ደግሞ ገና ወደ ሙላት ባልመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት እየተመላለሱ ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ሕይወትንና የሕይወት ውሳኔዎችን አስመልክቶ የሚኖረው የደቀመዝሙርነት ሂደት፣ በአንድ መንገድ እዚህ ባለችው መንግሥት ደግሞም ገና በምትመጣው መንግሥት አስተሳሰብ መሠረት የተቃኘ የመሆኑ ነገር ሞጋች በመሆኑ ዘወትር ያደራድረናል፡፡ [ዶ/ር ዲቪድ ባወር]*
>
> *በወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ ከመንደር ወደ መንደር በመዘዋወር “**የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ**” እያለ ሲሰብክ፣ በርካታ ነገሮችን እየተናገረ ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ፣ በእርሱ አማካይነት የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣቷን፣ በመካከላቸውም መሆኗን መናገሩ ነው፡፡ ይህንንም ሥልጣን በተሞሉ ትምህርቶቹ፣ ኢጋንንትን በማስወጣት በእነርሱ ላይ ባለሥልጣን መሆኑን በማሳየት፣ ደግሞም በፈውስ አገልግሎቱም*

*ጭምር አሳይቷል፡፡ ስለዚህም፣ ኢየሱስ የተናገረው የመጀመሪያ ነገር መንግሥቱና የንጉሡ ሥልጣን በእኔ አማካይነት፣ በመካከላችሁ ናት በማለት ነው፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ መንግሥት መጥታለች ሲል፣ መንግሥቷ በሙላቷ አልመጣችም፣ ሆኖም ወደ ፊት የእግዚአብሔር ንግሥና ለሁሉም በሚታይ መንገድ ይገለጣል ማለቱ ነው፡፡ እንግዲያው ኢየሱስ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች" ምን እያለ ነው? ስንል፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በመቅረቧ ምክንያት ሰዎችን ወደ ንስሓ በመጥራት፣ ሰዎች ራሳቸውን ለንጉሡ እንዲያስገዙ፣ በመገዛታቸውም፣ በመታዘዛቸውም፣ ንጉሡንም በመከተላቸው ከእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ ጋር ይተባበራሉ ወይም እንደገና የቤተሰቡ አካል ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ለንጉሡ የመገዛት ጉዳይ በንስሓ የሚገለጥ ነው ማለት ነው፡፡ [ዶ/ር ግሬግ ፐሬይ]*

በማቴዎስ 4፥18-22፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፡፡ ተምሳሊቱም ንጉሣዊው መሲህ የመንግሥቱን መሪዎች የሚመርጥ መሆኑ ነው፡፡

ይህንንም ተከትሎ፣ በማቴዎስ 4፥23-25 ውስጥ፣ ማቴዎስ የወንጌሉን ቀጣይ ሁለት አንጓዎች ወፍ በረር ዳሰሳ ይቀርባል፡፡ ኢየሱስ ሕዝቡን በመፈወስና በማስተማር በመላው ገሊላ መዘዋወሩን ያውጃል፡፡ ማቴዎስ 5-7 የኢየሱስን ትምህርት ሲገልፅ፣ ምዕራፍ 8-9 ፈውሱን ይገልፃል፡፡

ማቴዎስ በመንግሥቱ ወንጌል ላይ ያቀረበውን ትረካ ከተመለከትን፣ በማቴዎስ 5፥1-7፥29 ያለውን ተጓዳኝ ንግግር ደግሞ እንመልከት፡፡

## የተራራው ስብከት

ይህ ንግግር በዘልማድ የተራራው ስብከት ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ የመንግሥቱ ዜጎች ስለሚኖራቸው የጽድቅ ሕይወት ኢየሱስ ገልጧል፡፡ የመንግሥቱን ጉዳይ ብቻ ሰባት ጊዜ የጠቀሰ ሲሆን፣ ጠቅላላ መልእክቱም በዚህ መሪ ሃሳብ ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜም፣ የጽድቅ ተግዳሮት የይሁዲነት መምህራን ከሚያስቡት እጅግ የበለጠ መሆኑን ኢየሱስ አፅንዖት ሰጥቶበታል፡፡ የመንግሥቱ ዜጎች አባት በጣም የቀረበና አስበውት በማያውቁ መንገድ ሊባርካቸው መዘጋጀቱንም አፅዖት ሰጥቷል፡፡ ስብከቱን የተለየ ባሕርይ የሚሰጡት የእነዚህ ጥንድ ሃሳቦች ውህደት ነው፡፡

በምንዝርና ላይ ኢየሱስ የሰጠውን ትምህርት፣ ከተራራው ስብከት በምሳሌነት እንጥቀስ፡፡ የእግዚአብሔር ህግ ላይ ላዩን የሚነበበውን ከመፈፀም እና የአይሁድ መምህራን በተለምዶ ከሚያስተምሩት በላይ የሚጠይቅ መሆኑን ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

በማቴዎስ 5፥27-28 ኢየሱስ ምን እንደተናገረ እናድምጥ፡

> አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል።
> እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል። (ማቴ 5፥27-28)

ኢየሱስ "**እንደ ተባለ**" ሰምታችኋል የሚለውን ሲጠቅስ፣ በዚያን ዘመን በአይሁድ መምህራን መካከል ስለ ነበረው የቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም እያወሳ ነበር፡፡ ጥቂት መምህራን የብሉይ ኪዳን ህግጋት ዝሙትን እንደሚከለክሉ ያስተምራሉ፣ ሆኖም የሰውን ልብ መሠረታዊ ጉዳይ ማንሳት ይሳናቸዋል፡፡ ኢየሱስ ግን በብሉይ ኪዳንም እንኳን አንድ ነገር እውነት እንደነበር ያም ነገር እግዚአብሔር ውጫዊ ባህርይን ማረቅን ብቻ ሳይሆን፣ መታዘዙ ከልብ መጀመሩን እንደሚሻም አመልክቷል፡፡

*እኔ አንዳንድ ጊዜ ብሉይና አዲስን የሚቃረን አስተሳሰብ ያለን ይመስለኛል፡፡ ይህም የሚገለፀው፣ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ወጪያዊ ተግባራትን ይጠይቅ ነበር፣ ማለትም ሰዎች እንዲገረዙ፣ መስዋእት እንዲቀርብ፣ ቀናት ተለይተው እንዲከበሩ እግዚአብሔር ይጠብቃል፡፡ ያም ውጪያዊ ሃይማኖታዊ መገለጫዎችን ያሳያል፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን ጊዜው የልብ ሃይኖት ጉዳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ልባችንን ይፈልጋል፤ የውስጥ መነካታችንን ይፈልጋል እንላለን፡፡ አንድ ሰው የብሉይ ኪዳንን ጽሑፎች በቅርበት ሲመለከት፣ በተለይም የነቢያትን መልእክት ሲመለከት፣ ይህ አስተሳሰብ ይሠራል ብዬ አላምንም፡፡ ለምሳሌ፣ ለቢዩ ኢዩኤል፣ "ልባችሁን እንጂ፣ ልብሳችሁን አትቅደዱ" ብሎ ሲናገር፣ ውጪያዊ ሃይማኖትን በመቃወም ያቀረበው ቀጥተኛ ንግግር፣ ማለትም እግዚአብሔር በውጫዊ ነገራቸው ብቻ እንዲታዘዙት ሳይሆን፣ ልባቸውንም እንደሚሻ፣ ውስጣዊ ማንነታቸውንም እንደሚሻ፣ እነርሱን እነርሱ ያደረገውን ነገር እንደሚሻ ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም በመዝሙር 103 ይህንኑ ታያላችሁ፡፡ "ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ አጥንቶቼም ሁሉ፥ የተቀደሰ ስሙን።" ማለትም፣ ዘማሪው የእግዚአብሔር ህዝብ እርሱን እንዲባርኩ፣ እነርሱን እነርሱ ባደረገው ማንነታቸው ጌታን እንዲያመልኩት ጥሪ ያደርግላቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ የውስጣዊ መነካትን የሚጠይቀው ነገር በአዲስ ኪዳን እንጂ የልብ ሃይማኖት በብሉይ አልነበረም የሚለው አስተሳሰብ፣ እግዚአብሔር ከብሉይ ኪዳን ሕዝቡ ጋር የነበረውን የቃል ኪዳን ትስስር በፍትሃዊነት ያላገናዘበና መሠረታዊ እውነቱን ያልያዘ ነው፡፡* [ዶ/ር ማርክ ጊግኒላት]

የኢየሱስ ከልብ ስለሚነሳው መታዘዝ የሰጠው አፅንዖት የመንግሥቱን ዜጎች እንደ "**የዋህ**" በ5፥5፣ "**ጽድቅን እንደሚራቡና እንደሚጠሙ**" በ5፥6 እና እንደ "**ልበ ንፁሃን**" በ5፥8 ወደ መግለጡ አምርቶታል፡፡ በእርግጥ ኢየሱስ፣ ተከታዮቹ ይህን ወደ መሰለው ዜግነት መንግሥተ ሰማያት በሙላት ሳትመጣ ሙሉ በሙሉ ሊለወጡ እንደማይችሉ ያውቃል፡፡ ሆኖም ከዚያን ወዲህ ጻድቃን እንዲሆኑ ግድ ይላቸዋል፡፡ በማቴዎስ 5፥48 ምን እንደተናገረ አድምጡ፡

*እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ። (ማቴ 5፥48)*

በአንድ በኩል፣ ይህ ትዕዛዝ ለማሟላት የማይቻል ነው፣ ማለትም ማንም ሰው እንደ እግዚአብሔር ፍፁም አይሆንም፡፡ ይህ ግን ወደ ተስፋ መቁረጥ አይመራንም፡፡ በተቃራኒው፣ ኢየሱስ ጸጋን የተሞላና የሚያበረታታ ተስፋን ሰጥቶናል፡፡ በስብከቶቹ ሁሉ፣ መንግሥቱ አሁንም ለእኛ እንደሆነች ለታማኝ ተከታዮቹ አረጋግጦላቸዋል፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 5፥3-10 በሚገኘው አስደሳች ክፍል ውስጥ፣ ስምንት በረከቶችን እናገኛለን፡፡ በመካከል ያሉት ስድስቱ መንግሥተ ሰማያት በሙላት ስትመጣ የምንቀበላቸው ናቸው፡፡ የመጀመሪያውና የመጨረሻው በረከቶች ግን የተለዩ ናቸው፡፡ የእርሱ የሆኑት እነዚህን በረከቶች እንደተቀበሉ ኢየሱስ ተናግሯል፡፡

በማቴዎስ 5፥3፣10 ኢየሱስ እነዚህን በረከቶች የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።… ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። (ማቴ 5፥3፣10)***

ኢየሱስን የመከተሉ ትልቅ ተግዳሮት የእግዚአብሔር የመንግሥቱ ኃይል የመንግሥቱ ጻድቃን ዜጋዎች እንድንሆን እኛን የለወጠን መሆኑን ከሚናገረው ተስፋ ጋር ኢየሱስ አቻ አድርጎታል፡፡

በወንጌሉ የመጀመሪያ ዐቢይ አንጓ ውስጥ፣ ትኩረትን ወደ ኢየሱስ የአገልግሎት ዓላማና መልእክት በመሳብ ማቴዎስ በመንግሥቱ ወንጌል ላይ አፅንዖት ሰጥቷል፡፡ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያትን ወደ እግዚአብሔር ህዝብ ያመጣ መሲሃዊ ንጉሥ ነው፡፡ እርሱም ስለ መንግሥቱ የመለወጥ ኃይል አስተምሯቸዋል፡፡ በታማኝነት ከዘለቁም፣ መንግሥቱ በሙላት በምትመጣበት ወቅት ታላቅን በረከት እንደሚወርሱ ተስፋን ሰጥቷል፡፡

# የመንግሥቱ መስፋፋት

ሁለተኛው የማቴዎስ ወንጌል ዐቢይ አንጓ፣ በመንግሥቱ መስፋፋት ላይ ያተኩራል፡፡ ከማቴዎስ 8፥1 እስከ 11፥1 ድረስም ይዘልቃል፡፡

## የኢየሱስ ተዓምራትና የነበሯቸው ምላሾች

ስለ መንግሥቱ መስፋት የሚያወሳው ትረካ ከማቴዎስ 8፥1-9፥38 ድረስ ይዘልቃል፡፡ ስለ ኢየሱስ ተዓምራትና የተለያዩ ሰዎች ለተዓምራቱ የሰጡትን ምላሽ ይዟል፡፡

ይህ ትረካ በዐሥራ አንድ ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፣ ኢየሱስንና ለምፃሙን በ8፥1-4፣ የመቶ አለቃውን ልጅ በ8፥5-13፣ የጴጥሮስን አማት በ8፥14-17፣ ማዕበሉን በ8፥18-27፣ ሁለቱን አጋንንት ያደሩባቸውን በ8፥28-34፣ ሽባውን በ9፥1-8፣ ቀራጮችንና ኃጢአተኞችን በ9፥9-17፣ ልጃገረዲቷንና ሴቲቱን በ9፥18-26፣ ሁለቱን ዐይነ ስውራን በ9፥27-31 እና ሌላ አጋንንት ያደሩበትን በ9፥32-34 ውስጥ አካቷል፡፡ ከዚያም አንጓው የኢየሱስን ርኅራኄ በሚገልጸው በ9፥35-38 ይጠናቀቃል፡፡

በኢየሱስ ሕይወት ስለ ተከናወኑት ነገሮች ለመተረክ ጊዜ የሚፈቅድልን ለጥቂቶቹ ብቻ ነው፡፡ በ8፥1-4 ለምፃሙን፣ በ8፥5-13 የመቶ አለቃውን ልጅ፣ በ8፥14-17 የጴጥሮስን አማት፣ በ9፥1-8 ሽባውን፣ በ9፥20-22 ደም የሚፈሳትን ሴት እና በ9፥27-31 ሁለቱን ዐይነ ስውራን በመፈወስ የመንግሥቱን የመፈወስ ኃይል ገልጧል፡፡

በማቴዎስ 9፥18-26 የሞተችውን ልጅ ነፍሷን በመመለስ፣ በሞት ላይ እንኳን ሥልጣን ያለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በማቴዎስ 8፥23-27 ኢየሱስ በተፈጥሮም ላይ ሥልጣን ያለው መሆኑን ማዕበሉን ፀጥ በማድረግ አሳይቷል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ በማቴዎስ 8፥28-34 ውስጥ ኢየሱስ በሰይጣን መንግሥት ላይ ያለውንም ሥልጣን በመቃብር ይኖሩ ከነበሩ ሁለት ሰዎች ላይ አጋንንቶችን በማስወጣት፣ በ9፥32-34 ከዲዳ ሰው በማስወጣት ገልጧል፡፡ በ9፥9-17 ውስጥ ደግሞ ማቴዎስን እንደ ደቀመዝሙር መጥራቱ ኢየሱስ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመለክተን ትልቅ አንዱ ነው፡፡ ማቴዎስ የቀረጥ ሰብሳቢነት ሕይወቱን ትቶ አዲስ ሕይወትን እንዲጀምር ኢየሱስ ጠርቶታል፡፡ ይህም ከተዓምራት በምንም አይተናነስም፡፡ የቀራጮችና የኃጢአተኞቹ ለውጥ አስደናቂ ነው ይህንንም ማቴዎስ ወዲያውኑ ኢየሱስ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ወደሚቀመጥበት ድግስ በመሄድ የደስታቸውን ምክንያት ማጣጣምና ማብራራ በመቻሉ እንረዳለን፡፡

ማቴዎስ በኢየሱስ ኃይል ላይ ከማትኮሩ ባሻገር፣ ለኢየሱስ ኃይል ህዝቡ ይሰጥ የነበረውንም ምላሽ አትኩሮበታል፡፡ በቀላሉ ስናስቀምጠው፣ ተደንቀዋል፡፡ ይህንንም እንደ ማቴዎስ 8፥27፣34፤ 9፥8፣26 እና 33 በመሳሰሉት ውስጥ እናያለን፡፡ አድናቆታቸው ግን አብዛኛውን ጊዜ እንዲቃወሙት አድርጓቸዋል፡፡

ጥቂቶቹ ኢየሱስን የሚቃወሙት ባለማመን ነው፡፡ ሌሎቹ፣ በተለይም የአይሁድ መሪዎች በግልጽ ይከሱታል፡፡ በማቴዎስ 8፥34 እንደምናየው ደግሞ፣ ጥቂቶቹ ይፈሩታል፡፡ በማቴዎስ 9፥3 እንደምናየው ደግሞ ሌሎቹ ይፈራሉ ይንቀጠቀጡማል፡፡ በማቴዎስ 9፥14 እንደምናየው በኢየሱስ ላይ የነበረው ተቃውሞ ስህተት ቢሆንም እንኳን በዓላማ የሚደረግ ነበር፡፡ በማቴዎስ 9፥34 እንደምናየው፣ አንዳንዶቹም እውነት እንደ ሆነ በሚያውቁት ነገር ላይ ፈቅደው ኢየሱስን ይቃወሙታል፡፡

> ***አዲስ ኪዳንን ስንመለከት ከሚገጥሙን እንቆቅልሾች አንዱ፣ ሰዎች ተዓምራቱን በገዛ ዐይኖቻቸው እያዩ ክርስቶስን እንዴት ሊቃወሙ እንደቻሉ ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ሰዎች መደነቃቸውን ደግመው ደጋግመው ይናገራሉ፡፡ ለዚህ ጥያቄ አንግበን፣ ይህን እንዴት እንዳደረጉ ለመመልከት፣ ማቴዎስ 22፥29 ማየት ይገባናል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ በማለት ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ነግሯቸዋል፡፡ በዚያ አውድ ውስጥ፣ በተለይ ተናገረው ለሰዱቃውያን ነው፣ እንደማስበው ግን ለህጉ መምህራን፣ ለሰዱቃውያንም ተናግሮታል፡፡ ሰዎችን ስህተት አስተምረዋል፤ ስለሚመጣው መሲህ ይሰጡት የነበረው ትምህርት በስህተት ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ ከዚህም ነገር እኛ ዛሬ ትልቅ ትምህርት እናገኛለን፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል አዛብተው የሚያቀርቡ ሰዎች፣ በሰዎች ውስጥ የተሳሳተ ጥበቃን ይፈጥራሉ፡፡ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት በእስራኤል ውስጥ የሆነው ይኸው ነበር፡፡ መሲሁ እንደሚመጣ ይጠብቁ ነበር፣ ግን የሚጠብቁት ብሔራዊ ነፃ አውጪ ሆኖ የሚመጣወን ነበር፣ ማለት ይቻላል፡፡ እናም ኢየሱስ መጣ፡፡ ኢይተውት የማያውቁትን፣ ከዚያም በኋላ የማያዩትን ነገር ቢያደርግም እንኳን፣ መጨረሻቸው ተቃውሞ ነበር ምክንያቱም***

*መሪዎቻቸው በክርስቶስ ላይ የሚያስነሱት ተቃውሞ ተዓምራቶቹን ዋጋ የሚያሳጣ ነበርና ነው፡፡ እነዚህንም ነገሮች በማድረጉ ከሰይጣን ማህበር ውስጥ ይቀላቅሉት ነበር፡፡ ለዓመታት የዘለቁት፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገሩት እነዚህ የተሳሳቱ ትምህርቶች፣ በሃይማኖታዊ ሥልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች ተቃውሞ፣ የበርካቶች ልብ ተዓምራቱን እያዩ እንኳን ኢየሱስን እንዳይቀበል አድርጓቸዋል፡፡ [ቄስ ጂም ማፐልስ]*

በኢየሱስ ኃይለኛ ተዓምራት ላይ ማቴዎስ የሚያቀርበውን ትረካ የሚደመድመው ኢየሱስ ለመንጋው መራራቱን በገለጠበት በማቴዎስ 9፥36-38 ነው፡፡

***ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር።***
***ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።***
***በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤***
***እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው።***
***(ማቴ 9፥36-38)***

ህዝቡ እንደ ንጉሥ ካልተቀበሉባቸው ምክንያቶች አንዱ በአብዛኛዎቹ መሪዎቻቸው በመንገላታታቸውና በተሳሳተ መንገድ በመማራቸው መሆኑን ኢየሱስ ተረድቷል፡፡ ተዓምራቶቹ ደግሞ ልባቸውን እንዳለሰለሰውና ሊከተሉት እንዳዘነበሉም አውቋል፡፡ ስለዚህም የጠፉትን በምድር ወዳለችው የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያመጡ፣ በዚያም የመንግሥቱ ጻድቃን ዜጎች እንዲሆኑም የሚያስተምሩ ወንጌላውያንንና ትክክለኛ የሆኑ መሪዎችን እንዲያስነሳላቸው እግዚአብሔርን እንዲለምኑት ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው፡፡

## የንጉሡ መልእክተኞች

በመንግስቱ መስፋፋት ላይ ማቴዎስ ያቀረበውን ትረካ ከተመለከትን፣ በማቴዎስ 10፥1-11፥1 ወዳለው ንግግር ዘወር እንበል፡፡ ይህ ንግግር ደቀመዛሙርትን እንደ መልእክተኛ ወይም እንደ ንጉሡ ወኪሎች በመመልከቱ ላይ ያተኩራል፡፡

በዚህ ክፍል፣ ቀደም ባለው ትረካ ማብቂያ ላይ ኢየሱስ አንስቶት ለነበረው ጥያቄ ምላሽ ይሰጥበታል፡፡ ወንጌላውያንንና መሪዎችን እግዚአብሔር እንዲያስነሳላቸው እንዲለምኑት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ካዘዘ በኋላ፣ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት በማስታጠቅ የመንግሥቱን አገልግሎት ያስፋፋል፤ ልክ እርሱ እንደሚያደርገውም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በቃልና በሥራ መምጣቷን እንዲያውጁም አዟቸዋል፡፡

በማቴዎስ 10፥7-8 እንደምናነብበውም፣ እንዲህ ብሎ ልኳቸዋል፡

*ሄዳችሁም። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ።*
*ድውዮችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አውጡ፤*
*በከንቱ ተቀበላችሁ፥ በከንቱ ስጡ። (ማቴ 10፥7-8)*

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከመላኩ አስቀድሞ በርካታ ማስጠንቀቂያዎችን ሰጥቷቸዋል፡፡ የኢየሱስን ምሳሌነት ሲከተሉ ሕይወት ቀላል አትሆንም፡፡ ዓለምም አትመቻቸውም፡፡ መከራን ይቀበላሉ፡፡ ማላገጫ ይሆናሉ፣ ይታሰራሉ ደግሞም ይገደላሉ፡፡

ነገር ግን አገልግሎታቸው በሰማዩ አባታቸው የተባረከ እንደሚሆን እና በመጨረሻም የመንግሥቱ ደስታ የእነርሱ እንደሚሆንም ተስፋንም ሰጥቷቸዋል፡፡ በማቴዎስ 10፥39 ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ዋስትናን እንዴት እንደሰጣቸው አድምጡ፡

*ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል። (ማቴ 10፥39)*

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ስለ ኢሱስ ትምህርትና የፈውስ አገልግሎት ሲሉ የቀደመ ሕይወታቸውን ትተዋል፡፡ ሆኖም የመንግሥቱን ሕይወት ከንጉሡ ከኢየሱስ ከራሱ ጋር ሆነው እንደሚካፈሉ ግን ዋስትናን ሰጥቷቸዋል፡፡

በዚህ ሁለተኛው የወንጌሉ ዐቢይ አንጓ፣ በተለይም በኢየሱስ የኃይል አገልግሎት እና ለደቀመዛሙርቱ በሰጠው መመሪያ፣ የመንግሥቱን መስፋፋት ማቴዎስ እንደ ገለጠ አይተናል፡፡ እናም ይህ ነገር በዘመኗ ቤተክርስቲያን ለሚኖረን አገልግሎትም መልካም ምሳሌ ይሆነናል፡፡ በኢየሱስ ኃይል ላይ ስንደገፍና እንደታማኝ ደቀመዛሙርት ስናገለግለው፣ ኢየሱስ በእኛ አማካይነት መንግሥቱን ይመሠርታል በሰማያዊ በረከቶችም ይባርከናል፡፡

# ምልክቶችና ምሳሌዎች

የማቴዎስ ወንጌል ሦስተኛው አንጓ የንጉሡና የመንግሥቱ መገለጥ በምልክቶችና በምሳሌዎች መታየት መቀጠሉን ያሳየናል ይህም በማቴዎስ 11፥2- 13፥53 ውስጥ ይገኛል፡፡

## ምልክቶችና ምላሾቻቸው

ኢየሱስ ባሳያቸው ምልክቶችና ባስከተሏቸው ምላሾች ላይ ያተኮረው የማቴዎስ ትረካ ከማቴዎስ 11፥2-12፥50 ይዘልቃል፡፡ እነዚህ ምልክቶች ንጉሡና መንግሥቱ የመጡ መሆናቸውን እና ስለ መንግሥቱ የነበረውን የተሳሳተ አመለካከት ያቃኑ ነበር፡፡ በውጤቱም፣ ስር ይዞ የነበረው ነቀፋም ማደግና መስፋት ጀመረ፡፡

እነዚህ ተከታታይ ምእራፎች በአምስት የተከፈሉ ናቸው፡ በ11፥2-19፣ ምልክቶቹ እርሱ ብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች የፈፀመው መሲህ መሆኑን እንደሚያረጋግጡ እና ህዝቡም በንስሓ ለምልክጶቹ ምላሽ እንዲሰጡ እየጋበዘ እንደሆነ ኢየሱስ ለመጥምቁ ዮሐንስ ነግሮታል፡፡ በ11፥20-30፣ ተዓምራት

ያደረገባቸውን ከተሞችም በመንብኘት፣ ንስሓ የማይገቡትን ሲያስጠነቅቅ ወደ እርሱ ለመጡት እረፍትን ይሰጣል፡፡ በማቴዎስ 11፥30 እንዳስቀመጠው፡

***ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና። (ማቴ 11፥30)***

በ12፥1-21፣ ማቴዎስ ምዕራፎቹን የሚጀምረው በተለይ ፈሪሳውያን ለኢየሱስ ምልክቶች በሰጧቸው ምላሾች ላይ በማትኮር ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ሰንበት እግዚአብሔር ያለውን ዓላማ አስመልክቶ ከፈሪሳውያን ጋር ያደረገውን ክርክር የዘገበ ሲሆን የሰንበት ጌታ መሆኑንም በሰንበት አንድ ሰው በመፈወስ ማረጋገጡን ዘግቧል፡፡ ሰንበት ሕይወትን ለማዳንና ለፈውስ መሆኑን ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

በ12፥22-37፣ ህዝቡ በተዓምራቱ እየተደነቀ እንኳን፣ ፈሪሳውያን ኃይልህ የቢኤል ዜቡል ነው በማለት ነቅፈውታል፡፡ የህጉ መምህራን እርሱን እንደ መሲህ ከመቀበል ይልቅ፣ በአጋንንት እንደተያዘ አምነዋል፡፡

በ12፥38-50፣ ፈሪሳውያን በግብዝነት ሌላ ምልክት እንዲያሳያቸው ይጠይቁታል፣ ኢየሱስ ግን ከዮናስ ምልክት በቀር እንደማይሰጣቸው አስጠንቅቋቸዋል፡፡ ምልክቱ ምን ነበር? የዮናስ ከሦስት ቀናት በኋላ ከዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ መውጣት በነነዌ ያሉትን አህዛብ ወደ ንስሓ እንደመራቸው ሁሉ፣ የኢየሱስ ከሦስት ቀናት በኋላ ከሞት መነሣቱም ለበርካታ አህዛብን ወደ ንስሓ የሚመራ ይሆናል፡፡

ንስሓ በመግባት ወደ እርሱ የሚመጡትን የትኞቹንም ነገዶች የሚቀበል መሆኑን ለማሳየት፣ ኢየሱስ አይሁዳዊ እናቱና ወንድሞቹ ብቻ የእርሱ ቤተሰቦች አለመሆናቸውን እስከመናገር ደርሷል፡፡ ይልቁንስ፣ በማቴዎስ 12፥49-50 እንዲህ ብሏል፡

***እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ። እነሆ እናቴና ወንድሞቼ፤***
***በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ እኅቴም***
***እናቴም ነውና አለ። (ማቴ 12፥49-50)***

ኢየሱስ ያሳያቸው ምልክቶች የተመዘገቡበትን የማቴዎስ ትረካ ካየን፣ በማቴዎስ 13፥1-53 የተመዘገቡትን የኢየሱስን የመንግሥቱን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

## የመንግሥቱ ምሳሌዎች

ማቴዎስ እውቅ የሆኑትን ምሳሌዎቹን በአምስት ከፍሎ ዘግቦልናል፡፡ በ13፥1-23 የዘሪውን ምሳሌ፣ በ13፥24-30 የእንክርዳዱን ምሳሌ፣ የሰናፍጪን ቅንጣትና የእርሾውን በ13፥31-43፣ የተሰወረውን ሀብትና እንቁውን በ13፥44-45 እና የመረቡን ምሳሌ በ13፥47-53 ዘግቧል፡፡ ምሳሌዎቹም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የተሰጡ የተሳሳቱ ምሳሌዎችን ለማረም የተቀረፁ ነበሩ፡፡

በጥቂቶቹ ምሳሌዎች ውስጥ፣ ለምሳሌ በ13፥31-32 የሰናፍጪ ቅንጣት፣ የእርሾው ቁጥር 33፣ የሀብቱ በቁጥር 44 እና የእንቁው ከቁጥር 45-46 ውስጥ፣ መንግሥተ ሰማያት እጅግ የከበረ ዋጋ ያለው መሆኑንና የትኛውም ዋጋ ተከፍሎ ሊፈለግ እንደሚገባው ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ ጅማሬው ላይ ዋጋ ቢስ ይመስላል፣ አንድ ቀን ግን በሙሉ ክብሩ ይገለጣል፡፡

ኢየሱስ በተጨማሪም፣ እስራኤል ንጉሡንና መንግሥቱን ባለመቀበል በመውደቋ ላይ ያተኮሩ ምሌዎችንም ተናግሯል፡፡ በማቴዎስ 13፥1-23 የዘሪውን ምሳሌና ማብራሪያውን ሲሰጥ፣ ለማመን ብዙ እንቅፋቶች እንደሚኖሩና ብዙዎችም መንግሥቱን እንደማይቀበሉ ኢየሱስ ግልፅ አድርጓል፡፡

ይህም ሃሳብ በእንክርዳዱ ምሳሌ በቁጥር 24-30 እና 36-43 ደግሞም በቁጥር 47-51 በመረቡ ምሳሌዎች የበለጠ ተጠናክሯል፡፡ ብዙዎች መንግሥቱን እንደማይቀበሉና በመጨረሻም እንደሚጠፉ ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች ኢየሱስን ለሚቃወሙ ግልፅ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው፤ ለማያምኑት ንስሓ የሚገቡበትን እድል በመስጠት፣ የብቸኛው እውነተኛ ንጉሥ ተከታዮች እንዲሆኑ ይጋብዛሉ፡፡

*ክርስቶስ መጥቷል፡፡ ትንቢቶቹንም ፈፅሟል፤ መንግሥቱንም አምጥቷል፡፡ ሆኖም፣ ምልዐቱ ግን ገና ተጠብቋል፡፡ እኛም እንደ ክርስቲያኖች፣ ወደ መንግሥቱ ገብተናል፣ ሆኖም ዘወትር ቅድሚያዎቻችንን መመዘን፣ እርሱንም እንደሚገባ ባልተከተልንበት ንስሓ መግባት፣ ሕይወታችንንም እንደ ፈቃዱ በታማኝነት መምራታችንን ማረጋገጥ፣ የመንግሥቱ ዋና ከሆኑት ከእሴቶቹ ጋር በመጣጣም ከእርሱ ጋር መስማማት ይገባናል፡፡ ስለዚህም፣ ዘወትር ንስሓ ልንገባ ይገባናል፣ ወደ እርሱም እንደ ነቢይ፣ እንደ ካህንና እንደ ንጉሥ በማወቅ ልንመጣ ይገባል፡፡ በዚህም ዓለም የእርሱን ዓላማዎች ለማስፈፀም በሚያስችል መንገድ ልንከተለው እና ልናገለግለው እንችላለን፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

*ክርስቲያኖች የመንግሥቱን መምጣት እንዲናፍቁና እንዲፈልጉ እናበረታታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በግል ደረጃ፣ የመንግሥተ ሰማያት ሥልጣን ኃይላችን ነው፡፡ ይህም ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ፣ እግዚአብሔርን ያማከለ ሕይወት እንድንኖር ያበረታታናል፣ ስለዚህም፣ በሕይወታችን የእግዚአብሔር ሥልጣን መገለጡ የመንፈሳዊ ሕይወታችን ግብ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ የመንግሥተ ሰማያትን ፅንሰ ሃሳብ በቤዛዊ ታሪክ አውድ ልንረዳው ይገባናል፡፡ በዚህም የቤዛዊ እቅዱን አጀማመሩን፣ እድገቱን እና አፈጻፀሙን እንረዳለን፡፡ ከዚያም የመንግሥተ ሰማያት አስተምህሮዎች ብሉይንና አዲስን አንድ የሚያደርጉ መሆኑን እናያለን፡፡ ቤዛችን የሆነውን የእግዚአብሔርን ዋና ዓላማ እንድናይና በቀላሉም እንድንረዳ ያስችሉናል፡፡ ሦስተኛ፣ መንግሥተ ሰማያት ትክክለኛ የሆነውን ንፅረተ-ዓለም ያስጨብጠናል እና ሁሉም የእግዚአብሔር መሆኑን እንድናስተውል ይደርገናል፡፡ መንግሥቱም ወደ ምልዐቱ ይመጣል፣ በምድር ያሉትንም ክፉ ኃይላት ይፈርድባቸዋል ይጠራርጋቸዋልም ምክንያቱም እርሱ ሉዓላዊ ንጉሥ ነውና፡፡ ስለዚህ፣ እኛ ለራሳችን ብቻ አንኖርም፡፡ ለጎረቤቶቻችን፣ ለማኅበረሰባችን እና ለመላውም ዓለም ደኅንነት ግድ ይለናል፡፡ ለእኛ ቅርብ ወይም ሩቅ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ ትኩረትን እንሰጣለን፡፡ ወደ ማኅበረሰቡም ውስጥ በመግባት ሁሉንም በሚገባው መጠን ማደስን ኃላፊነታችን እናደርጋለን፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ቻን፣ የተተረጎመ]*

## እምነትና ታላቅነት

አራተኛውና በእምነትና በታላቅነት ላይ ያተኮረው የማቴዎስ ወንጌል ዐቢይ አንጓ ከ13፥54 ይጀምርና እስከ 18፥35 ይዘልቃል፡፡ ይህ አንጓ በመንግስቱ ውስጥ ወደ ታላቅነት ደረጃ የሚደርስ የኢየሱስ ታማኝ ደቀመዝሙር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልጣል፡፡

## በኢየሱስ ማመንን መቃወም

የዚህ ክፍል ትረካ ከ13፥54 -17፥27 የሚዘልቅ ሲሆን፣ እምነትን በኢየሱስ ላይ ሙሉ በሙሉ ማድረግን ከአንዲት ሴት በስተቀር ሁሉ መቃወማቸውን የሚዘግቡ ዐሥራ ሦስት ምዕራፎች አሉት፡፡

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች በኢየሱስ ማመን ሙሉ በሙሉ ተቃውሞ በደረሰበት ሁለት ወቅት ላይ ያተኩራል፡፡ መጀመሪያ፣ በ13፥54-58 ኢየሱስ ወደ ገዛ ከተማው ወደ ናዝሬት ሲመጣ፣ የቀደሙት ወላጆቹ በእርሱ ተዓምራት የማድረግ ችሎታ ላይ አልተሟገቱም፡፡ ሆኖም አሁንም ይቀወሙትና ያጠቁት ነበር፡፡ በ13፥58፣ ናዝራውያን ከእምነታቸው ማነስ የተነሣ በርካታ ተዓምራትን አላዩም፡፡

ከዚያም፣ 14፥1-12 ስለ ሄሮድስና ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ሞት ይነጋራል፡፡ ሄሮድስ በዮሐንስ ላይ ከሠራው ሥራ የተነሣ የእግዚአብሔር ፍርድ የገባው ነበር፡፡ ከዚህ በላይ ግን፣ ቁጥር 1 ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ ተዓምራት እንዳልተከራከረ ያብራራልናል፡፡ ይልቁኑም፣ አማካሪዎቹ ኢየሱስ በሄሮድስ ላይ ችግር ለመፍጠር ከሞት የተነሣው መጥምቁ ዮሐንስ ነው ብለው አምነዋል፡፡

ቀጣዮቹ ሦስት ምዕራፎች በኢየሱስ ደቀመዛሙርትና በእምነት ማደግ እንዴት እንዳስፈለጋቸው የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ማቴዎስ 14፥13-21 ኢየሱስ አምስት ሺዎችን የመገበበት ታሪክ ነው፡፡ ደቀመዛሙርቱ እርሱን የተከተሉትን እንዲመግቡ ኢየሱስ ይነግራቸዋል፣ በቁጥር 15 ግን ደቀመዛሙርቱ ያለን ምግብ ትንሽ ነው በማለት በጥርጣሬ ይመልሱለታል፡፡ ስለዚህም፣ ኢየሱስ ምግቡን በመባረክ አምስት ሺዎችን እንዲመግብና እንዲትረፈረፍ በማድረግ ኃይሉን አረጋገጠላቸው፡፡

በ14፥22-36፣ ኢየሱስ በውሃ ላይ ተራመደ፡፡ በመጀመሪያ፣ ጴጥሮስ ከታንኳው ላይ በመውጣት በኢየሱስ ያለውን እምነት አሳየ፣ ሆኖም አደጋውን ሲመለከት በባህሩ ውስጥ መስጠም ጀመረ፡፡ ኢየሱስም ካዳነው በኋላ፣ በቁጥር 31 ላይ፣ "**አንተ እምነት የጎደለህ ስለ ምን ተጠራጠርህ**?" ሲል ነቀፈው፡፡

ምዕራፍ 15፥1-20 በኢየሱስና በፈሪሳውያን መካከል ስለተደረገ ግጭት ይተርክልናል፡፡ ኢየሱስ የተናገረውን በጣም ቀላል ነገር እንዲያብራራለት ጴጥሮስ ጠየቀ፡፡ ስለዚህም፣ በቁጥር 16፣ ኢየሱስ መልሶ "**እናንተ እስካሁን የማታስተውሉ ናችሁን**?" አላቸው፡፡

በ15፥21-28፣ ከእነዚህ ትዕይንቶች ሁሉ በዚህኛው ብቻ ሴት ልጇ በአጋንንት የተያዘችባት ከነዓናዊት ሴት በኢየሱስ በብርቱ ስታምን እናገኛለን፡፡ ከሌሎቹ በተቃራኒው፣ ኢየሱስ እንዲረዳት ትለምነዋለች፡፡ በቁጥር 28 ደግሞ "**አንቺ ሴት፣ እምነትሽ ታላቅ ነው!**" በማለት ኢየሱስ አስረግጦ ይነግራታል፡፡

ማቴዎስ ከዚህ በኋላ ወደ ኢየሱስ ደቀመዛሙርት ደካማ እምነት ይመለሳል፡፡ በ15፥29-39፣ አራት ሺህ ሰዎች ስለተመገቡበት ታሪክ ይጽፋል፡፡ በቁጥር 33፣ ምንም እንኳን ቀደም ብለው አምስት ሺዎችን መመገቡን ቢያውቁም በቂ ምግብ ከየት እናገኛለን በማለት ደቀ መዛሙርቱ ይጠይቃሉ፡፡

በ16፥1-12፣ ኢየሱስ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ጋር ይከራከራል፡፡ አንድ ነጥብ ላይ፣ ወደ ደቀመዛሙርቱ ዘወር በማለት "**ከፈሪሳውያን እርሾ**" እንዲጠበቁ ሲያስጠነቅቃቸው፣ እንጀራ ይዘው ስላልመጡ እንደተናደደባቸው አሰበዋል፡፡ ኢየሱስ ግን ለሺዎች እንጀራን የመገበበትን ወቅት አስታወሳቸውና በቁጥር 8 ላይ ደቀመዛሙርቱን "**እናንተ እምነት የጎደላችሁ**" ብሎ ጠራቸው፡፡

ይህንንም ተከትሎ፣ ሁለት በብርቱ የሚዛመዱ ትዕይንቶችን እናገኛለን፡፡ በአንድ በኩል፣ በ16፥13-20 ውስጥ የጴጥሮስን የታወቀ የእምነት መግለጫ እናገኛለን፡፡ በ16፥16 ላይ፣ ኢየሱስን "**አንተ ክርስቶስ፣ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ**" በማለት ጴጥሮስ አውጇል፡፡ ኢየሱስም ጴጥሮስን ስለ እምነቱ አመስግኖታል ባርኮታልም፡፡

በሌላ በኩል ግን፣ በ16፥21-27 ውስጥ፣ ኢየሱስ ጴጥሮስን በብርቱ ገስፆታል፡፡ ስቃይንና ሞትን ለመቀበል ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ ለደቀ መዛሙርቱ ይነግራቸው ጀመር፡፡ ጴትሮስ መቃወም ሲጀምር፣ በቁጥር 23 ውስጥ፣ "**ሂድ አንተ ሰይጣን**" በማለት በብርቱ መልሶለታል፡፡ ጴጥሮስ እንደ ሰው እንጂ እንደ እግዚአብሔር እያሰበ እንዳልሆነ ኢየሱስ አብራርቷል፡፡

ይህንን ተግሳፅ ተከትሎ፣ በ17፥1-13 ወደምናገኘው የኢየሱስ መለወጥ እንመጣለን፡፡ ደቀመዛሙርቱም ኢየሱስን በክብሩ ሲያዩት፣ ዳስ በዚያ ለመሥራት ፈለጉ፡፡ በቁጥር 12 ግን፣ የእርሱ እውነተኛ ክብር የሚታየውከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ብቻ እንደ ሆነ ኢየሱስ አሳሰባቸው፡፡

በ17፥14-23 ውስጥ፣ በአጋንንት ስለ ተያዘ ወጣት እናነባለን፡፡ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለማስወጣት ሞክረው አልተሳካላቸውም፡፡ ኢየሱስ ግን ካስወጣው በኋላ፣ በቁጥር 20 ውስጥ፣ "**እምነት ያነሳችሁ**" ብሏቸዋል፡፡

በመጨረሻም፣ በ17፥24-27 ውስጥ፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ወደ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መጥተው ኢየሱስ ለመቅደሱ ግብር ስለ መክፈሉ ጠየቋቸው፡፡ ጴጥሮስም ፈጥኖ፣ ምናልባትም በፍርሃት፣ ኢየሱስ እንደሚከፍል ተናገረ፡፡ ቆይቶም ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ በመምጣት ገንዘብ ጠየቀው፣ ኢየሱስም በተዓምር ገንዘቡን ሰጠውና ጴጥሮስ ሊጨነቅ እንደማይገባው አብራራለት፡፡

ማቴዎስ ኢየሱስን ስለተቃወሙት እና ስላመነችበት ከነዓናዊት ሴት ቢጠቅስም፣ ዋና ትኩረቱ ግን ደቀመዛሙርቱ በእርሱ ላይ ባላቸው እምነት በማደጋቸው አስፈላጊነት ላይ ነበር፡፡

ማቴዎስ እንደገና፣ በ18፥1-35 ውስጥ የኢየሱስን ትምህርቶች መተረኩን ይቀጥላል፡፡ ትምህርቱ የሚያተኩረው በእግዚአብሔር መንግሥት ቤተሰብ ውስጥ ስለ ሚገለጠው እውነተኛ ትልቅነት፣ ማለትም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ወንድሞችንና እህቶችን በትህትና ከማገልገል ስለ ሚገኘው ትልቅነት ማለት ነው፡፡

## ታላቅነት በመንግሥቱ ቤተሰብ ውስጥ

ባለፈው ምዕራፍ የመጨረሻ አንጓ ውስጥ፣ ኢየስስ ስለ እርሱ ተከታዮች የንጉሡ የእግዚአብሔር ልጆች፣ በማለት ተናግሯል፡፡ ይህም መግለጫ ማቴዎስ ይህንን የወንጌሉን ክፍል በጥያቄ እንዲጀምር መርቶታል፡፡ በማቴዎስ 18፥1 እንደምናነብበው፡

*"በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?"(ማቴ 18፥1)*

ኢየሱስም ለዚህ ጥያቄ መልስ የሰጠው መመሪያዎችን ከምሳሌዎች ጋር በማቀላቀል በአራት ዋና ክፍሎች ከፍሎ ነው፡፡ ኢየሱስ በመጀመሪያ በ18፥2-4፣ ደቀመዛሙርቱ እንደ ሕፃናት በየዋህነት እንዲኖሩ አሳስበቸዋል፡፡

ከጠላቶቹ በሚደርስበት ተቃውሞ ፊት በመቆም፣ ደቀ መዛሙርቱ እንደ እግዚአብሔር ልጆች እንዴት በመንግሥተ ሰማያት ሊኖሩ እንደሚችሉ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አስተምሯል፡፡ የመንግሥቱ የወደፊት ምልዓት እንዳልመጣ ያውቃል፡፡ ለእግዚአብሔር ልጆችም ከጠላቶች እና ከኃጢአት ጋር መጋደል የሕይወታቸው ክፍል መሆኑንም ያውቃል፡፡

በቁጥር 5-14 ውስጥ፣ ሰማያዊ አባታቸው ስለ ጠፋው በግ ግድ እንደሚለው ሁሉ እነርሱም ስለ ደካሞች ግድ እንዲላቸው ደቀ መዛሙርቱን አስተምሯል፡፡ በማቴዎስ 18፥10፣14 ውስጥ ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

***"ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና። ...እንደዚሁ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም።" (ማቴ 18፥10፣14)***

ኃጢአት ግንኙነታቸውን በሚያውክ ወቅት ተከታዮቹ እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ እርስ በርስ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሲያሳስባቸው፣ በማቴዎስ 18፥15-20 ውስጥ ሃሳቡን ገንብቶ አሳይቷል፡፡ ከቁጥር 21-35 ውስጥ፣ ሰማያዊ አባታቸው ይቅር እንዳላቸው እንዲሁ የበደላቸውን "ወንድማቸውን" ይቅር እንዲሉ አሳስቧል፡፡

በእኛም ዘመን የእግዚአብሔር ክብር እየጨመረ መጥቷል፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንግሥቱን በዚህ ምድር ለማስፋት በርካታ ተዓምራትን እያደረገ ስለ ሆነ ነው፡፡ በኢየሱስ ዘመን ግን ይህ

ማለት በእግዚአብሔር ላይ የሚደርሰውም ተቃውሞ ይጨምራል ማለት ነው፡፡ ምስጋና ይግባውና፣ በትግሎቻችን፣ በአስቸጋሪ ጊዜዎቻችን እና በፈተናዎቻችን ውስጥ የሚያግዙንን በርካታ የከበሩ ስጦታዎች እግዚአብሔር ሰጥቶናል፡፡ ከነዚህም ስጦታዎች ውስጥ ጽናት፣ ሰላምና የእርሱን ከእኛ ጋር አብሮነት ይገኛሉ፡፡ በጣም የከበረውም ስጦታ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለ እኛ ግድ ይለዋል ይጠብቅናልም፣ ድካማችንን ይረዳል ይገባዋልም፡፡ በተጨማሪም የሚወድዱንንና የሚያገለግሉንን ሰዎችንም ሰጥቶናል፡፡ እነርሱም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉ ወንድሞችና እህቶች፣ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡

# የአሁን ተቃውሞና የወደፊት ድል

የማቴዎስ ወንጌል አምስተኛ ዐቢይ አንጓ መሪ ሃሳብ መንግሥተ ሰማያት አሁን ስለ ሚደርስበት ተቃውሞ እና ስለ ወደፊቱ ድል የሚያወሳው ነው፡፡ ይህ ትረካ ከ19፥1--22፥46 ይዘልቃል ኢየሱስም በሕይወቱ በዚህ እርከን ላይ ምን ዓይነት ታላቅ ተቃውሞ እንደገጠመው ያሳየናል፡፡

## የማያባራ ተቃውሞ

እነዚህ ምእራፎች በኢየሱስ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረቱ ሦስት ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ በ19፥1-20፥46 ውስጥ፣ ኢየሱስ በይሁዳ ተቃውሞ ይገጥመዋል፡፡ በዚያም ከፈሪሳውያን ስለ ፍቺ ጥያቄ ይቀርብለታል፡፡ ከዚያም ስለ ሀብትና ስለ ኃይል ከነበረ የተሳሳተ መረዳት ከመነጨ ተቃውሞ ጋርም ይጋፈጣል፡፡

በወንጌሉ ጅማሬ ላይ፣ በኢየሱስና በአይሁድ መሪዎች መካከል የነበረውን የውጥረት ጅማሬ ማቴዎስ ዘግቦታል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ፣ ጠላትነቱ በሙላት ማደጉን ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ፣ ፈሪሳውያን አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስን ለማጥመድ ሆን ብለው ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፣ ይህንንም በማቴዎስ 9፥3-8፤ 21፥15፣23 እና 22፥15-40 እናያለን፡፡

አንድ ምሳሌ ለማየት፣ በማቴዎስ 22፥15 ላይ ማቴዎስ ምን እንደዘገበ አድምጡ፡

> *ስለዚህ ፈሪሳውያን ሄዱና እንዴት አድርገው በነገር እንዲያጠምዱት ተማከሩ። (ማቴ 22፥15)*

በተመሳሳይም ጊዜ፣ ኢየሱስ አንዳንድ ጊዜ የአይሁድን መሪዎች ይሞግታቸዋል፡፡ ይህንንም በሁለቱ ልጆች ምሳሌ ውስጥ፣ በጭሰኛ ገበሬዎች እና ስለ ጋብቻ ድግስ በማቴዎስ 21፥28-22፥15 ሲያነሳ እናየዋለን፡፡

ግጭቱ ግን ዘወትር እንዲያው በቃላት ልውውጥ ብቻ የሚያባራ አልነበረም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቀጥታ እና ኃይል የቀላቀለም ይሆን ነበር፡፡ ይህንንም በማቴዎስ 21፥12-16፣ ኢየሱስ የሻጮችን ገበታ ሲገለብጥ እናያለን፡፡ በ23፥13-35 የተመዘገቡት ሰባቱ የእርግማን ወዮዎች የጠነከሩ ዱላዎች ነበሩ፡፡

በማቴዎስ 23፥15 ኢየሱስ እንዴት እንደ ገሰፃቸው አድምጡ፡

> *እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ፥ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት፥ ወዮላችሁ። (ማቴ 23፥15)*

እርግጥ ነው፣ በእነዚህ ምእራፎች ውስጥ የነበሩት ገፀ-ባህርያት ኢየሱስና ፈሪሳውያን ብቻ አልነበሩም፡፡ ለምሳሌ በ21፥1-11 በምናገኘው በሆሳዕና እለት ኢየሱስን ህዝቡ አሁንም እንደሚያከብረው ሲያዩ የአይሁድ መሪዎች ጥላቻቸው አገርሽቶባቸዋል፡፡

በእነዚህ ክፍሎች ሁሉ ደቀመዛሙርቱ ፍልሚያውን በልቡናቸው እንዲይዙ ኢየሱስ አበረታትቷቸዋል፡፡ በማቴዎስ 19፥27-30፣ አንድ ቀን ከእርሱ ጋር በክብር እንደሚቀመጡ ተስፋ ሰጥቷቸዋል፡፡ በ20፥17-19 ግን፣ እነዚህ የክብር ቀናት የሚመጡት ግን ስቃይ ከሞላበት ሞቱ በኋላ መሆኑንም አስጠንቅቋቸዋል፡፡

ከዚያም በበለጠ፣ ደቀመዛሙርቱ ወደ ክብር የሚደርሱት ትህትና ከሞላበት መከራ በኋላ መሆኑንም ኢየሱስ አሳስቧል፡፡ ኢየሱስ ይህንን ነጥብ ወደ እነርሱ ያመጣው ለሦስት ጊዜያት ነው፡፡ በማቴዎስ 19፥30 ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡

> *ነገር ግን ብዙዎቹ ፊተኞች ኋለኞች፥ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ። (ማቴ 19፥30)*

ከዚያም በማቴዎስ 20፥16 ውስጥ፣ እንዲህ ብሏል፡

> *እንዲሁ ኋለኞች ፊተኞች፥ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ፤ (ማቴ 20፥16)*

ይህንንም በማቴዎስ 20፥26-28፣ እንዲህ ሲል ደግሞታል፡

> *በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ*
> *የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥*
> *ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤*
> *እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ*
> *እንዲያገለግሉት አልመጣም። (ማቴ 20፥26-28)*

የኢየሱስ መንግሥት እንግዳ ይመስላል፡፡ ተከታዮቹ መከራ ይቀበላሉ፣ የእስራኤል ንጉሥ ራሱም በእስራኤል ሰዎች ይገደላል፡፡ ከድል በፊት ግልፅ ሽንፈት ይገጥመዋል፡፡

የከረረው ተቃውሞ ቀጣይ ክፍል በ20፥17-34 የምናገኘውን የኢየሱስን ወደ ኢየሩሳሌም መግባት ያካትታል፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም መከራነ ለመቀበልና ለመሞት እንደሚሄድ ኢየሱስ ግልፅ አድርጓል፡፡ ተቃውሞ የገጠመው ሁለት ደቀመዛሙርት ልጆቿን በመንግሥቱ ሥልጣን ላይ እንዲያስቀምጥላት

ከፈለገች ሴት ብቻ ነበር፡፡ ከዚያ ግን፣ ኢየሱስ በድል ወደ ከተማዪቱ ሲገባ የብሉይ ኪዳንን ትንቢት በመፈፀሙ የኢየሩሳሌም ህዝብ በክብር ተቀብሎት ነበር፡፡

በሚቀጥለው አንጓ፣ በ21፥12-22፥46 ግን፣ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባና ሲወጣ ደግሞም በመቅደስ ውስጥ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡ ስለ ሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ እያስጠነቀቃቸው፣ የሻጮችን ገበታ ገለበጠ፡፡ ከዚያም በበለጠ፣ ኢየሱስና የሃይማኖቱ መሪዎች ለቄሳር ግብር ስለመክፈል፣ ስለ ሙታን ትንሣኤ፣ ስለ ታላቂቱ ትዕዛዝና ማሲሁ የማን ልጅ ስለ መሆኑ ነገረ መለኮታዊ ሙግት አድርገው ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን በማቴዎስ 22፥46 እንደምናየው ተቃዋሚዎቹን ልክ አገባቸው፡፡

> ***አንድም ቃል ስንኳ ይመልስለት ዘንድ የተቻለው የለም፥ ከዚያ ቀንም ጀምሮ ወደ ፊት ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም። (ማቴ 22፥46)***

መንግሥተ ሰማያትን በሚገጥመው በማያባራው ተቃውሞ ላይ የማቴዎስን ትረካ ከዳሰስን፣ አሁን ደግሞ ከእርሱ ጋር የተያያዘውን ትምህርት እንመለከታለን፡፡

## የወደፊት ድል

ይህ ክፍል ከማቴዎስ 23፥1-25፥46 ይዘልቃል፡፡ በዚህ ትምህርቱ፣ ኢየሱስ የመንግሥተ ሰማያትን የወደፊት ድል ገልጧል፡፡

ይህ ክፍል በማቴዎስ 23፥1-38 በተፃፈውና የኢየሱስ ተቃዋሚዎችን በሚጠብቃቸው ወዮዎች አዋጅ ይጀምራል፡፡ ይህ ትምህርት በተለይ በፈሪሳውያን ላይ ማለትም፣ በሃሰት አስተምህሯቸው፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ በማንገላታታቸው እና በግብዝነታቸው ላይ ያተኩራል፡፡

በዚህ ትምህርት መደምደሚያ ላይ፣ በማቴዎስ 23፥37-38 ስለ ኢየሩሳሌም የሚሰማውን ስሜት ኢየሱስ እንዲህ ጠቅለል አድርጎ አስቀምጦታል፡

> ***ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም።***
> ***እነሆ፥ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። (ማቴ 23፥37-38)***

የሚቀጥለው የኢየሱስ ትምህርት ክፍል የደብረ ዘይት ተራራ ትምህርት በመባል የሚታወቅ ሲሆን በማቴዎስ 24፥1-25፥46 ውስጥ ይገኛል፡፡ በተለምዶ የደብረ ዘይት ተራራው ስብከት ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት፣ ንግግሩን ያደረገው ከደቀመዛሙርቱ ጋር በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ስለ ነበረ ነው፡፡

የደብረ ዘይት ተራራ ትምህርት በሦስት ተቀዳሚ ክፍሎች የተከፈለ ነው፡ በ24፥4-28 ውስጥ፣ መንግሥተ ሰማያት ወደ ምድር የምትመጣበትን የምጥ ጣር መጀመሪያ እንግዳ ዘመን ኢየሱስ ሲገልጥ በሙሉ ክብሯና ኃይሏ ግን እንዳልተገለጠች ተናግሯል፡፡

በ24፥29-31 ውስጥ፣ ስለ መንግሥቱ ሙላት፣ የሰው ልጅም በደመና እንደሚመጣ እና መንግሥተ ሰማያትም በሙሉ ኃይልና ክብር እንደምትመጣ ተናግሯል፡፡

ከዚያም በ24፥32-25፥46 ውስጥ፣ ያ የክብር ቀን መቼ እንደሆነ ማንም ስለማያውቅ የራሱ ህዝብ በንቃት እንዲጠብቅ ኢየሱስ አሳስቧል፡፡

> *እንግዲህ፣ ኢየሱስ የሚመለስበትን ጊዜ አስመልክቶ፣ ልናስብ ከሚገባን አልፈን በምንም መንገድ በዚህ እና በዚያ ቀን ነው ብለን እንዳንገምት በዓላማ ተናግሯል፡፡ ሰዓቲቱንና ቀኑን ማንም አያውቅም ብሏል፡፡ እርሱ እንኳን በሰውነቱ ዘመን የመመለሻውን ቀን አያውቅም፡፡ ስለዚህ ነገሩን በማጥበብ ብንገምትና ብናስብ ኢየሱስን አለመታዘዝ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በተስፋ አንጠባበቅም፣ አንጓጓም፣ የመምጣቱንም ምልክቶች አንመረምርም ማለት አይደለም፡፡ በአዲስ ኪዳን የኢየሱስ ዳግም መምጣት አስተምህሮ ተቀዳሚ ዓላማ እኛን ማረጋጋት፣ ለማበረታታት፣ ተስፋችንን ለማደስ፣ ወደ ተቀደሰ ሕይወት ለመምራት እና የክርስቶስን መመለስ እንድንጠባበቅ ለማድረግ ነው፡፡ ቁርጥ ያለውን ጊዜ ባናውቅም እንኳን፣ በሚመለስበት በየትኛውም ሰዓት እርሱን በጉጉትና በደስታ ለመቀበል ዘወትር ዝግጁ ልንሆን ይገባናል፡፡ [ዶ/ር ኤሪክ ቶኔስ]*
>
> *እርሱ እንደሚመለስ ሙሉ በሙሉ ልንተማመን ይገባናል፡፡ ተመልሶ በመምጣትም የጀመረውን ሁሉ ወደ ሙላት እንደሚያመጣው ልንተማመን ይገባናል፡፡ ታማኞችም ልንሆንም ይገባናል፡፡ ሆኖም ግን በሐዋርያት ሥራ 1 ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንደተገለጠው ዓይነት አጠባበቅ ሊሆን አይገባም፣ ዐይናቸውን አሻቅበው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ መላእክት፣"እይናችሁን አንስታችሁ ወደ ሰማይ ስለምን ትምለከታላችሁ? ወንጌልን ለፍጥረት ወደ ማድረስ ሥራ ተሰማሩ" አሏቸው፡፡ እርሱ ተመልሶ ይመጣል፣ እኛ ግን ታላቁን ተልዕኮ ይዘን መሮጥ ይገባናል፡፡ ንጉሡ ተመልሶ እንደሚመጣ ለህዝቦች ሁሉ በማወጅ በንጉሡ አገልግሎት ውስጥ መጠመድ ይገባናል፡፡ እርሱ ተመልሶ ይመጣል፡፡ ንስሓ ግቡ በወንጌልም እመኑ በማለት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ወደ መንግሥቱ የተጨመሩትንም ደቀ መዛሙርት ልናደርግ፣ ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር በሚያስችል ሕይወት እንዲያድጉ ወይም እርሱን እንዲመስሉ ልናደርግ ይገባናል፡፡ በሕይወታችን ሁሉ እርሱን በሚያስከብር ሕይወት ልንኖር የእርሱንም መመለስ ዘወትር በመጠባበቅ በየዘመናቱም ከቤተክርስቲያን ጋር "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና!" ልንል ይገባናል፡፡ [ዶ/ር ስቴፋን ዌሉም]*

በዚህ በአምስተኛው የወንጌሉ አንጓ፣ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን እንደተቃወሙት፣ ሊገድሉትም እንዳቀዱ ማቴዎስ ዘግቧል፡፡ ኢየሱስ ግን በዓለም የሚመከር የጥኛውም ምክር የመንግሥቱን የወደፊት ክብር እንደማያስቀር ግልፅ አድርጓል፡፡ ያም ትክክል መሆኑን ታሪክ አረጋግጧል፡፡

የአይሁድ መሪዎች ገድለውታል፡፡ መንግሥቱ ግን በየዘመናቱ ማደጉን ቀጥሏል፡፡ አንድ ቀንም፣ የመጨረሻውም ክፍል ትክክል መሆኑን ታሪክ ያረጋግጣል፡፡ ኢየሱስ፣ በሙሉ ኃይልና በታላቅ ክብር፣ ምንግሥቱንም በሙላት ለማምጣት እና የእርሱን ታማኝ ህዝቦችም በመንግሥቱ ላዕላይ በረከት ብድራታቸውን ሊከፍል ይመለሳል፡፡

# የኢየሱስ አገልግሎት መደምደሚያ

የማቴዎስ ወንጌል ትረካ መደምደሚያ ከማቴዎስ 26፥1-28፥20 ይዘልቃል፡፡ በዚህ ስፍራ፣ የኢሱስን አገልግሎት መደምደሚያ የሚገልጠው መሲሃዊው ንጉሥ በመታሰሩ፣ በመሰቀሉና በትንሣኤው ነው፡፡

የማቴዎስን ወንጌል መደምደሚያ ስንመረምር፣ በማቴዎስ የመንግሥት አፅንዖት ላይ በሚያተኩሩ ሦስት ርዕሰ ሃሰቦች ላይ እናተኩራለን፡፡ እነርሱም፡ የግጭት ሃሳቦች፣ ደቀመዝሙርነትና ድል ናቸው፡፡ አስቀድመን ወደ ግጭቱ ሃሳብ እንመለስ፡፡

## ግጭት

ኢየሱስ ይዞ የመጣው መንግሥት አይሁድ መሲሁ ይዞ ይመጣል ብለው ከሚጠብቁት መንግሥት እጅግ የተለየ ነበር እናም ይህ ጉዳይ ከኢየሱስና ከመንግሥቱ ጋር ወደ ቀጥተኛ ግጭት አስገብቷቸዋል፡፡ እንደተመለከትነውም፣ ግጭቱ በማቴዎስ ወንጌል ሁሉ ውስጥ ይስተዋላል፣ የሚደመደመው ግን በማጠቃለያው ትረካ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በ26፥3-4፣ አይሁድ በኢየሱስ ላይ ሲያሴሩ፤ የሚያዝበትንና መከራ የሚቀበልበትን ሲቀይሱ በ26፥14-16፣ በቁጥር 47 እና በቁጥር 57-68 እና ስቀለው እያሉ በጮኹበት በ27፥20-25 ውስጥ እንመለከታለን፡፡ ነገሩ ይፋ የሚወጣውም አይሁድ ራሳቸው የኢየሱስን መሰቀል ኃላፊነቱን ሲወስዱ ነው፡፡ በማቴዎስ 27፥25 ማቴዎስ ምን እንደጻፈ አድምጡ፡

> ***ሕዝቡም ሁሉ መልሰው። ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ። (ማቴ 27፥25)***

ኢየሱስም በመስቀል ላይ ሲያጣጥር፣ አይሁድ አላገጡበት፣ የእስራኤል መሲሃዊ ንግሥ ነኝ በማለቱም ተሳለቁ፡፡ ይህንንም በማቴዎስ 27፥41-42 እናነባለን፡

> ***እንዲሁም ደግሞ የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሎች ጋር እየዘበቱበት እንዲህ አሉ።***
> ***ሌሎችን አዳነ፥ ራሱን ሊያድን አይቻለም፤ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ፥ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እናምንበታለን። (ማቴዎስ 27፥41-42)***

አይሁድ በእግዚአብሔር ላይ ተሳድቧል በማለትና ለዙፋኑም አሳፋሪ ነው በማለት ኢየሱስን ተቃወሙት፣ እውነታው ግን ሊያድናቸው የሚችል ብቸኛ ኃይል ያለውን ንጉሥ መቃወማቸው ነው፡፡

ከተቃውሞውም ባሻገር፣ በማቴዎስ ማጠቃለያ በመንግሥቱ ውስጥ የደቀመዝሙርነት ርዕሰ ሃሳብም አትኩሮት ተሰጥቶታል፡፡

## *ደቀመዝሙርነት*

ማቴዎስ መከራ የሚቀበልን መሲህ መከተል ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ አፅንዖት ሰጥቶበታል፡፡ ይህንንም ጫን ብሎ የገለጠው በኢየሱስ አገልግሎት ወሳኝ በሆነው በዚህ ወቅት የደቀመዛሙርቱን ውድቀት ሲዘግብ ነው፡፡ በማቴዎስ 26፥14-16 እና በቁጥር 47-50 ይሁዳ አሳልፎ ሲሰጠው፣ በ27፥3-10 ደግሞ በዚህ ውድቀቱ ምክንያት ራሱን ሲሰቅል እናያለን፡፡ በ26፥36-46 ደግሞ በጌተሰማኒ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ ከእርሱ ጋር በታማኝት መትጋት ሲሳናቸው እናያለን፡፡ ጴጥሮስ ደግሞ አላውቀውም ብሎ ሲክደው በ26፥69-75 እናየዋለን፡፡ በመጨረሻም፣ በ26፥56 ውስጥ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሁሉም ትተውት ይሄዳሉ፡፡

እውነታውም ኢየሱስን መከተል በጣም ከባድ መሆኑ ነው፡፡ መከራ የተቀበለውን መሲህ እናምናለን እኛም እንደ እርሱ መከራን እንድንቀበል ጠርቶናል፡፡ ለእርሱ የምንታመን ከሆንን፣ እኛም ችግርንና መከራን እንቀበላለን ያም ለመውደቅ ይፈትነናል፡፡ መንግሥተ ሰማያት ገና በሙላት አልመጣችም፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ያልሆኑ ብዙ ገፅታዎች ገና ይኖራሉ፡፡

የግጭትንና የደቀመዝሙርነትን ሃሳብ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ መንግሥቱ ድል እንሸጋገራለን፡፡

## ድል

የድሉ ሃሳብ በይፋ የወጣው በኢየሱስ ትንሣኤ ሲሆን፣ ይህም መሲሃዊው ንጉሥ የህዝቡን ጠላቶች፣ ሞትንም ጨምሮ ድል የማድረጉ ማረጋገጫ ነው፡፡ በተጨማሪም የድልን ሃሳብ በዕርገቱ ወቅት ኢየሱስ በተናገራቸው የመጨረሻ ንግግሮችም ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ የመጨረሻ ንግግር የሚገኘው በማቴዎስ 28፥18-20 ውስጥ ሲሆን፣ በተለምዶም ታላቁ ተልዕኮ ተብሎ ይጠራል፡፡ እነርሱም ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው የመጨረሻ መመሪያዎች፣ እርሱ በሌለበትም ለሚሰጡት አገልግሎት የተላኩባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ መመሪያዎች የሚጀምሩት ክርስቶስ ስለ መንግሥቱ ሥልጣን በመናገር መሆኑን መጥቀስ ይገባል፡፡ እስኪ በማቴዎስ 28፥18 ኢየሱስ ያወጀውን እናድምጥ፡፡

> ***ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። (ማቴ 28፥18)***

> ***ሙሉ ግዛት፣ ሙሉ ኃይል ደግሞም በሕጋዊነት ሊቀበል የሚገባው ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ በነገራችንም ላይ፣ የእርሱ ኃይል የፍቅር ኃይል ስለሆነ አፍራሽ አይደለም፡፡ ማለትም በፍቅር የሚቀሰቀስ ኃይል ማለት ነው፡፡ በፍቅር የተቀባ ኃይል ማለት ነው፡፡ ኢያችሁ፣ ፍቅር ብቻ ቢኖራችሁ፣ ጥሩ ስሜት ሊኖራችሁ ይችላል ኃይል ከሌላችሁ ግን ምንም ነገር የማትለውጡ***

*ትሆናላችሁ። ያለ ፍቅርም ኃይል ብቻ ካላችሁ ደግሞ አጥፊ፣ ገዳይና በጥላቻ የተሞላችሁ ትሆናላችሁ። ፍቅርንና ኃይልን በአንድነት ያጣመረ መለኮታዊ ልዕቀት ብቻ ነው። **"እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ስለወደደ አንድ ልጁን ላከ።"** በዚህች ፕላኔት በምድር ላይ ተመላልሶ ኃጢአት ያላደረገ እርሱ ብቻ ስለሆነ፣ በፍፁምም ስላልተታለለ፣ ኃይል ሁሉ ሊሰጠው የተገባው እርሱ ብቻ ነው። የተገደለ፣ የሞተ፣ የተቀበረ እና መልሶም የተነሣ እርሱ ብቻ ነው። እናም፣ እርሱ የትንሣኤ ጌታ ነው። ይህም የሰው ልጅ አዲስ ታሪክ ጅማሬ ብሥራት ነው። ለአህዛብም ተሰፋን አምጥቷል። ስለዚህም የእግዚአብሔር መንግሥት በብርቱ ኃይል በሥራ ላይ ናት፣ ዓለምን በወንጌል የመድረሱና ደቀ መዛሙርትን የማፍራቱም ሥራ የሚመሠረተው በዚህ ላይ ነው፣ እኔም **"ታላቅ መሠረት"** ብዬዋለሁ። ያለ ታላቅ መሠረት ታላቅ ተልዕኮ ሊኖር አይችልም። እርሱም ይህንን **"እነሆ እኔ እስካለም ፍፃሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ"** በሚል ታላቅ ተሰፋ ከድኖታል። እናም ኢየሱስ ጌታ፣ ኢየሱስ ንጉሥ፣ ሥልጣን ሁሉ የእርሱ የሆነ ገዢ፣ ስለሆነ እኛም ልንሄድ፣ ደቀመዝሙር ልናደርግ፣ ልናስተምር እና የእርሱን አገዛዝና ኃይል ልናውጅ ይገባናል። [ዶ/ር ፒተር ኩስሚክ]*

ሥልጣን ሁሉ ድል ለነሣው ጌታ ይገባዋል። አይሁድ ተቃውመውታል፤ ሮማውያን ሰቅለውታል አላግጠውበታልም። መቃብር ግን ሊይዘው አልቻለም እናም ትንሣኤ ለመሲሃዊው ንጉሥ ታላቅ ድል ነው። በእርሱም፣ መንግሥተ ሰማያት ወደ ምድር መጥታለች። የማቴዎስም ወንጌል የምሥራች ያ ነው።

የማቴዎስን ወንጌል ዳራ፣ ውቅርና ይዘት መርምረናል፣ አሁን ደግሞ፣ ማቴዎስ አፅንዖት የሰጠባቸውን ዋና ዋና ሃሳቦች እንዳስሳለን።

# ዋና ዋና ሃሳቦች

በትምህርታችን በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ትኩረታችንን ማቴዎስ በወንጌሉ አፅንዖት በሰጠባቸው በሁለት ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እናደርጋለን። እነርሱም የኢየሱስ መንግሥትና ወንጌል የብሉይ ኪዳን ቅርስ እና ኢየሱስ መንግሥቱን ያመጣላቸው የእግዚአብሔር ህዝብ ናቸው።

በኢየሱስ መንግሥትና ወንጌል የብሉይ ኪዳን ቅርሶች ላይ ማቴዎስ በሰጠው አፅንዖት እንጀምር።

## የብሉይ ኪዳን ቅርስ

*ብሉይ ኪዳን ምን ያህል የኢየሱስን መምጣት ተስፋ ያደርግ እንደነበር ማወቁ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ የማቴዎስ ወንጌል አስደናቂ ዘገባ ነው። ኢየሱስ ወደ መድረኩ ሲወጣ፣ በሥጋ የተገለጠው እስራኤል ነው። ወደ ግብፅ ወርዷል። ወደ ሚፈተንበት ወደ ምድረ በዳም ተወስዷል። ወደ ተራራም በመውጣት ህጉንም እንደገና ሰጥቷል። እነዚህ የአዲሱ ሙሴ ወይንም በሥጋ የተገለጠው እስራኤል ምስሎች፣ ምንጫቸውንና የመሆን አቅማቸውን የሚያገኙት ከብሉይ ኪዳን ነው። ምክንያቱም እስራኤል ስትጠራ፣ በእግዚአብሔር ስትመረጥ፣ መመረጧ፣ ለብቻዋ ደስ እንድትሰኝበት አልነበረም። ለአህዛብ ሁሉ በረከት ሆና*

*የምትገለጥበት፣ ኃላፊነቷ ነበር፡፡ ሆኖም ግን፣ በእስራኤል ረጅምና የኃጢአት ድራማዊ ታሪክ ምክንያት፣ ላራሷም ሆነ ለሌሎች መንግሥታት እንደተጠራችበት መሆን አልቻለችም፡፡ ስለዚህም፣ አሁን እንደ እግዚአብሔር ልጅ፣ በሥጋ እንደተገለጠው እስራኤል፣ ለራሷ እና ለአህዛብ መሆን ላቃታት ለእስራኤል ምትክ ሆኖ የተገለጠውን ኢየሱስን አገኘን፡፡ እንደማስበውም፣ እርሱን እዚህና እዚያ በጥቅሶች ውስጥ ከማሳደድ ይልቅ ብሉይ ኪዳን ምን ያህል ኢየሱስን በናፍቀት ይጠባበቅ እንደነበር በግሩም አወቃቀር የበለፀገ፣ ጥልቀት ያለው ንባብ፣ እንድናገኝ አስችሎናል፡፡ የእስራኤል የተሟላ ታሪክ፣ የእስራኤል መመረጥ እና የእስራኤል ውድቀት የኢየሱስ መምጣት እንዲናፈቅ አድርጎታል፣ ማቴዎስ በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምስት ወይንም ስድስት ምዕራፎች ይህንን በማንሳት አሳይቶናል፡፡ [ዶ/ር ማርክ ጊግኒላት]*

ከሁሉም በላይ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር በማይቋረጥ ፍቅር ስለ መተሳሰሩ የሚያወሳ ነው፡፡ ከእርሱ ጋር በበረከት እንድንኖር የተሰጠውን ተስፋ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ መሆኑን የሚናገር ታሪክ ነው፡፡ ማቴዎስም የእግዚአብሔር ትውልዶች የቀደሙትን ተስፋዎች ሊታመኑ እንደሚገባ እና በእነርሱም ዘመን በኢየሱስ አማካይነት እግዚአብሔር በሥራ ላይ መሆኑን እንዲያምኑ የሚናገረው ለዚህ ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን የመሲሃዊ ንጉሥነት እና አገልግሎት ለመደገፍ ሲል ማቴዎስ በልበ ሙሉነት ብሉይ ኪዳንን የሚጠቅሰው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

የብሉይ ኪዳንን የኢየሱስ መንግሥትና ወንጌል ቅርስ የገለጠባቸውን የማቴዎስን መግለጫዎች በአምስት መንገዶች በአጭሩ እንዳስሳለን፡፡ እነርሱም፡ ማቴዎስ ያጣቀሳቸው የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች እና ተዘዋዋሪ መግለጫዎች፣ በመንግሥተ ሰማያት ላይ የሰጠው አፅንዖት፣ ኢየሱስን እንደ መሲሃዊ ንጉሥ መግለጡ፣ ከማያምኑ የአይሁድ መሪዎች ጋር ኢየሱስ የነበረው ግጭት እና የኢሱስ ትህትናና ጨዋነት ናቸው፡፡ ባመቴዎስ የብሉ ኪዳን ማጣቀሻዎችና ተዘዋዋሪ ንግግሮች እንጀምር፡፡

## ማጣቀሻዎችና ተዘዋዋሪ ንግግሮች

ከሌሎቹ የወንጌላት ፀሐፊዎች በበለጠ ብሉይ ኪዳንን የጠቀሰ ማቴዎስ ነው፡፡ ማቴዎስ ብሉይ ኪዳንን ያጣቀሰባቸውን ትክክለኛ ብዛቶች አስመልክቶ ምሁራን ክርክር አላቸው ሆኖም በእርግጠኝነት ግን ቢያንስ 40 ጊዜ አጣቅሷል፣ በበርካታ ሌሎች ወቅቶችም በተዘዋዋሪ ጠቅሷል፡፡

ማቴዎስ ይህንን ለማስተላለፍ የሚጠቀምበት አንዱ ስልት **"የተባለው ይፈጸም ዘንድ"** የሚለውን ሐረግ በመጠቀም ነው፡፡ ማቴዎስ ይህንን ሐረግ የሚጠቀመው በኢየሱስ ሕይወትና በብሉይ ኪዳን መካከል ግልፅ ግንኙነት ለለመስረት ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 8፥17 ማቴዎስ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***በነቢዩ በኢሳይያስ። እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ (ማቴዎስ 8፥17)***

ከዚህ የብሉይ ኪዳን ማጣቀሻ ቀደም ብሎ፣ በርካታ የኢየሱስን ፈውሶች ማቴዎስ ዘግቧል፡፡ አንባቢዎቹ ኢየሱስ ፈዋሽ መሆኑን እንዲረዱ ብቻ ግን አልነበረም፡፡ ይልቁኑም፣ ኢየሱስ ሰዎችን የሚፈውሰው የብሉይ ኪዳንን ተስፋዎች ለመፈፀም መሆኑን እንዲያውቁ ነበር የሚፈልገው፡፡

*ለማቴዎስ ወሳኝ የሆነው አተያይ፣ የእኛም አተያይ ሊሆን ይገባዋል እላለሁ፣ ያም ኢየሱስ ሰዎች ሲናፍቁትና ሲጠብቁት የነበረው የምትመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ ነው የሚለው ነው፡፡ ስለዚህም፣ በታሪካዊ ካርታ ላይ መሲሁ የተነገረውን ሁሉ አንድ በአንድ ያሟላዋል ብለው ብለው ባይጠብቁም፣ ነፃነትን፣ መፈታትን፣ ተሃድሶንና ድነትን ይጠብቁ ነበር፡፡ ብሉይ ኪዳንም የእግዚአብሔር መንግሥት ስትመጣ፣ የምትገለጠው በአን ሰው፣ በመሲሁ አማካይነት መሆኑን፣ በዚያም አዋጅ ውስጥ፣ የእግዚአብሔር አገዛዝ ይጀምራል፣ በብሉይ ኪዳን የተነገረው የተሃድሶ፣ የድነትና የበረከት ተስፋም በፍሬ ይገለጣል፡፡ እናም፣ ሐዋርያት በጠቅላላ፣ ማቴዎስ ደግሞ በግሉ፣ የተነገሩትን ሁሉ ማን ያሟላቸው ይሆን? በማለት ሰንጠረዥ በጭናቸው ላይ በማኖር ዝም ብለው አልተቀመጡም፡፡ ይልቁኑ፣ በሥራዎቹና በአስተምህሮዎቹ፣ በባህርዩ እና ስለ እርሱ በተነገረው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት የምትገለጥበትን አንድ ሰው ይመለከቱ ነበር፡፡ በእርግጥም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በኢየሱስ ውስጥ ነበረች፣ በእርሱ መታወጅ ብቻ ሳይሆን መጥታም ነበር፡፡ በኢየሱስ ሲገለጥ ካየው ኃይል፣ አስተምሮና ሥራ በመነጨ መንገድም፣ ሐዋርያው ማቴዎስ ወደ ብሉይ ኪዳን መለስ በማለት ኢየሱስ በብሉይ ምን ያህል ይጠበቅ እንደነበረ አመልክቷል፡፡ በኢየሱስ ከተገለጠው ነገር በመነሳት ብሉይ ኪዳናቸውን ሲያነብቡ፣ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፣ በእርግጥም፣ ስለ እርሱና ስለ እርሱ ብቻ ይመሰክሩ እንደነበር ተረድተዋል፡፡ እናም፣ ብሉይ ኪዳንን ስናነብብ፣ የይሁዲነትን መነፅር በዐይናችን አጥልቀን ሳይሆን፣ ከክርስቶስ፣ የወንጌላት ማእከላዊ መልእክት ከሆነው እና የእግዚአብሔር መንግሥት በአካል መገለጥ ከሆነው ከራሱ ጋር በግል እንደተገናኘ ሰው ሊሆን ይገባዋል፡፡ [ቄስ ሚካኤል ግሎዶ]*

ሁለተኛውና ስለ ኢየሱስ ብሉይ ኪዳናዊ ቅርስ ማቴዎስ አፅንዖት የሰጠበት መንገድ በመንግሥተ ሰማያት ላይ የሰጠው አፅንዖት ነው፡፡

## መንግሥተ ሰማያት

በብሉይ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ህዝቡን እንደሚባርክ ተስፋን ሰጥቷል፤ በረከቱም በዳዊት ንጉሣዊ ልጅ አማካይነት እንደሚመጣ ተናግሯል፡፡ በኢየሱስ የተገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት በረከትም የነዚህ ጥንታዊ ቃል ኪዳናት ፍፃሜ መሆኑን ማቴዎስ አውጇል፡፡

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ፣ ኢየሱስም ራሱ ለሰዎች ይህንን እውነታ አሳስቧቸዋል፡፡ አዘውትሮም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለገባቸው ተስፋዎች ታማኝ መሆኑንም አዘውትሮ አስተምሯል፡፡ ምንም እንኳን መከራ ቢያስከትልና የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የተናገሩትን ሁሉ ባያከናውንም፣ ኢየሱስ መንግሥቱን እንደ መልካም የምሥራች ያቀረበው በዚህ መንገድ ነበር፡፡ ስለዚህ ህዝቡ በብሉይ ኪዳን የተነገረውን የእግዚአብሔር ቃል፣ ያም ኢየሱስ ዳግም ተመልሶ የጀመረውን ሁሉ

ሊፈፅም እንደሚገባው በሙላት ሊያምኑ እንደሚገባ አሳስቧል፡፡ በስተመጨረሻ ተመልሶ በመምጣት እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠውን ሁሉ ይፈፅማል፡፡

በእርግጥም፣ ብሉይ ኪዳን የሚያመለክተውን የመንግሥተ ሰማያትን ምስል በልበ ሙሉነት እየጠቀሰ ደቀመዛሙርቱ በብሉይ ኪዳን እንዲያምኑ የሚጋብዘው በዚህ መሠረት ላይ ሆኖ ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች እርስ በርስ እንዲዋደዱና እንዲያገለግሉ ያዘዛቸውም በዚያው መሠረት ነው፡፡

የምድርና የሰማይ አምላክ ታሪክን ሁሉ የሚቆጣጠር እና ተስፋውንም ሁሉ የሚፈፅም የመሆኑ እውቀት በየዘመናቱ የሚገኙ የእርሱን ሕዝብ እኛንም ጨምሮ፣ በክርስቶስ የሰጠን ተስፋዎች መልካም መሆናቸውን እንድንታመንባቸው ያደርገናል፡፡ አንድ ቀንም እግዚአብሔር ሁሉን አዲስና ትክክል እንደሚያደርግ እንድናምን ያነቃቁናል፡፡ እናም እግዚአብሔር መንግሥቱን በሙላት እንደሚያመጣ በትዕግሥት የምንጠባበቅበትን ብርታትም ይሰጡናል፡፡

ማቴዎስ ስለ ኢየሱስ መንግሥትና ወንጌል ብሉይ ኪዳናዊ ቅርስ አፅንዖት የሰጠበት ሦስተኛው መንገድ ኢየሱስ ይጠበቅ የነበረው መሲሃዊ ንጉሥ መሆኑን መግለፅ ነው፡፡

## መሲሃዊ ንጉሥ

ይህንን ሃሳብ ቀደም ብለን ስለ ኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ባነሳንበት ክፍል ውስጥ ጠቅሰነዋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎቹ የወንጌል ፀሐፊዎች በአንድነት ከጠቀሱት በበለጠ መንገድ ማቴዎስ ደጋግሞ "**የዳዊት ልጅ**" በማለት ኢየሱስን በመጥራት አሳይቶናል፡፡ ማቴዎስ በተጨማሪም ለኢየሱስ በርካታ ንጉሣዊ ማእረጎችን ማለትም፣ የአይሁድ ንጉሥ፣ የእስራኤል ንጉሥ፣ ንጉሣችሁ እና ንጉሥ ሰጥቶታል፡፡ ከዚህም በላይ፣ ማቴዎስ ንጉሣዊ ማእረግን የተጠቀመባቸው አንዳንድ ጥቅሶች በሌሎች ወንጌላት አይታዩም፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 2፥2፣ ይህንን የጠቢባኑን ጥያቄ ማቴዎስ ጠቅሷል፡

> ***የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? (ማቴ 2፥2)***

የትኛውም ወንጌል ይህንን ጥቅስ አላካተተም ወይም በኢየሱስ መሲሃዊ ንግሥና ላይ ይህን የመሰለ አፅንዖት አልሰጠም፡፡

ስለ ኢየሱስ መንግሥትና ወንጌል ብሉይ ኪዳናዊ ቅርስ የሚያወሳውና የምንጠቅሰው አራተኛው አፅንዖት ኢየሱስ ከማያምኑ የአይሁድ መሪዎች ጋር ያጋጠመው ግጭ ነው፡፡

## የማያምኑ የአይሁድ መሪዎች

የማቴዎስ ቀደምት አንባቢዎች ኢየሱስ ከአብዛኞቹ የአይሁድ መሪዎች ጋር በመጋጨቱ ኢየሱስ እውነተኛው መሲህ አይሆንን በማለት ለነበራቸው ጥርጣሬ ማረጋገጫ ሳይሆናቸው አይቀርም፡፡

ይህን ግምት እንዳይዙ ለማድረግ፣ የአይሁድ መሪዎች ታማኝ አለመሆን ሳያግደው እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ መጠበቁን ማቴዎስ ግልፅ አድርጎታል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜም፣ የፈሪሳውያንንና የህጉን መምህራን አስተምህሮ ይቃወም ነበር፡፡ በማቴዎስ 9፥14-17፣ ላይ ስለ ፆም፣ በ12፥1-13፣ ስለ ሰንበት፣ እና በ15፥1-20 ስለ እጅ መታጠብ የነበሯቸውን አመለካከቶች አርሟል፡፡ አብዛኛዎቹ የተራራው ስብከቶች በተለይም በ5፥17-48 የተጠቀሰው አይሁዳዊያን ስለ እግዚአብሔር ህግ ያላቸውን አስተሳሰብ ኢየሱስ የዚያ ህግ ፍፃሜ ከመሆኑ ጋር አነፃፅሮ አቅርቦታል፡፡

*መልካም፣ አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ በተራራው ስብከት ውስጥ “**እንደተባለ ሰምታችኋል፣ እኔ ግን እላችኋለሁ ...**” በማለት ሲናገር፣ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የተነገረውን እንደተቃረነ በማሰብ ሰዎች ይደነቃሉ፡፡ እኔ እንደማስበው ይህንን ስታነቡ የምትመለከቱት ግልፅ ነገር ግን እግዚዘብሔር የተናገራቸው የብሉይ ኪዳን ህግጋት በተለያዩ ፀሐፍትና መምህራን ከዘመን ወደ ዘመን የተሰጣቸውን ትርጓሜ ነበር ያረመው፡፡ ኢየሱስም የእግዚአብሔርን ህግ በትክክል የሚተረጉምና በህጉ የተፃፈውንም በማንሳት በእርሱ ዘመን ከነበሩ አድማጮቹ ጋር የሚያዋህድ እንደሆነ አድርጎ ራሱን አቀረበ፡፡ [ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት]*

*ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ላይ “**እንደተባለ ሰምታችኋል፣ እኔ ግን እላችኋለሁ ...**” የሚለውን ሐረግ ሲጠቀም፣ የብሉ ኪዳን ሕግ ተሻረ ማለቱ አይደለም፡፡ እንዲያውም፣ በግልፅ የተናገረው ተቃራኒውን ማለትም “**የመጣሁት ህግን ልፈፅም ነው**” ነበር ያለው፡፡ ኢየሱስ ያደረገው፣ የዘመኑ መምህራን የአስተምህሯቸውን ሥልጣን ለማረጋገጥ ይጠቅሷቸው እንደ ነበሩ መምህራን እርሱም በእርሱ ዘመን የነበረውን መጥቀስ ነበር፡፡ “**በልማዳችሁ ሰዎች እለ ህጉ ያሉትን ሰምታችኋል፣ እኔ ግን እላችኋለሁ ...**” ያም በዘመኑ ሥልጣን፣ በተጨማሪ ሥልጣን ይረጋገጣል፡፡ እናም፣ ኢየሱስ አስተምህሮውን በዚህ እውቅ የማስተማር ቴክኒክ ላይ ይመሠርተዋል፡፡ ይህንንም የብሉይ ኪዳንን ህግ ውድ ለማድረግ ሳይሆን፣ እጅግ ወሳኝ የሆነውን ነገረ-መለኮታዊና ክርስቶሳዊ እውነት ለመናገር ፣ ያም “**የብሉይ ኪዳንን ህግ ከእኔና ስለ ህጉ እኔ ከማስተምረው ጋር በማዛመድ ልትተረጉሙት ይገባል**” ለማለት ነበር፡፡ [ዶ/ር ግሬግ ፔሪ]*

*ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን ጋር አልተቃረነም፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ካየናቸው መሪ ሃሳቦች አንዱ ኢየሱስ አዲሱ ሙሴ እና ከሙሴም የሚልቅ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ፣ በሙሴ አማካይነት የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል የሆነው ብሉይ ኪዳን ተገልጦልናል፣ ኢየሱስ ግን የህጉ ሉዓላዊ ተርጓሚ ሆኖ ተገልጧል፡፡ በተራራው ስብከት ያየነው አብዛኛው ነገር ሙሴ ሲል የፈለገውን ትክክለኛ ትርጓሜ የሚወክል ነው፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስ “**አትግደል**” የሚለውን ትዕዛዝ አልደመሰሰም፡፡ እርሱ ያብራራልን ግድያ የሚጀምረው በልባችን በሚፈልቅ ቁጣ መሆኑን ነው፡፡ ያ ክፍል እንዴት እንደሚጀምር ታስታውሳላችሁ? ኢየሱስ፣ “**እኔ ህግን ልፈፅም እንጂ ልሽር አልመጣሁም**” ብሏል፡፡ እኔ እንደማስበው ህጉ በትክክል*

*ተተረጎመ ማለት ነው፡፡ በዚያ ኢየሱስ የተሟገተው፣ እርሱ የህጉን እውነተኛ መሻት ያሟላ በመሆኑ ላይ ነው፡፡ ህጉ ሊተረጎም የሚገባው ከክርስቶስ መምጣት፣ ከሞቱ፣ ከትንሣኤውና ከአገልግሎቱ አንፃር ነው፡፡ እርሱን በዚህ መንገድ ስንረዳው፣ ኢየሱስ ብሉይ ኪዳንን ሊፈፅም እንጂ ሊሽር እንዳልመጣ እናውቃለን፡፡ [ዶ/ር ቶማስ ሽሬነር]*

ኢየሱስ በእውነት የብሉይ ኪዳንን ጥበቃ አሟልቷል፡፡ በርካታ አይሁድ ግን ከብሉይ ኪዳን ጋር የማይገጥመውን የራሳቸውን መሻት ስላላሟላ ተቃውመውታል፡፡ የእነርሱ መሳሳትም ኢየሱስን መከተል ለሚፈልጉ ሁሉ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ የእኛ ሃሳቦች የእግዚአብሔር ሥራ እንዲህ ይመስላል ብሎ ወደ ማሰብ በቀላሉ ሊወስዱንና በራእያችን ላይ ጥላ ሊያጠሉ እንደሚችሉ ያስጠነቅቁናል፡፡ እግዚአብሔር ሊያደርግ በሚችለው ነገር ላይ ሰው ሠራሽ ገደብ ከማኖር ይልቅ እርሱ ተስፋችንንና ግምቶቻችንን ሊቀርፃቸው እንደሚገባው ያስጠነቅቀናል፡፡

ማቴዎስ በኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ቅርስ ላይ የሰጠው አምስተኛ አፅንዖት በግልፅ የሚታየን ስለ ኢየሱስ ትህትናና ጨዋነት በሰጠው መግለጫ ውስጥ ነው፡፡

## ትህትናና ጨዋነት

በኢየሱስ ዘመን የነበሩ አይሁድ እንደ ብሉይ ኪዳን አገላለጥ፣ ህዝቡን ነፃ ለማውጣት እግዚአብሔር ብርቱ ተዋጊ እንደሚልክ የተነገረውን በትክክል ተረድተዋል፡፡ የእግዚአብሔር አስደናቂ ነፃ አውጪነት ለህዝቡ ባለው ጨዋነት የሞላበት ትህትና ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማቴዎስ ጫን ብሎ ገልጧል፡፡ ይህንንም ነጥብ የመሠረተው ብሉይ ኪዳንን በመጥቀስ ነው፡፡

ለአብነት ያህል፣ በማቴዎስ 11፥29 ውስጥ፣ ኢየሱስ ሸክም የከበደባቸውን በነዚህ ቃላት ጠርቷቸዋል፡

*ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ (ማቴ 11፥29)*

በዚህ ስፍራ፣ ኢየሱስ የጠቀሰው ከኤርምያስ 6፥16 ሲሆን በዚያም መሲሁ ለህዝቡ ዕረፍትን ይሰጣል፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ በማቴዎስ 12፥15-21፣ የኢየሱስን ርኅራኄ የሞላበት አገልግሎት ከኢሳያስ 42፥1-4 በመጥቀስ ማቴዎስ አብራርቷል፡፡

በማቴዎስ 12፥19-20 ስለ ኢየሱስ የተሰጠውን መግለጫ አድምጡ፡

*አይከራከርም አይጮህምም፥ ድምፁንም በአደባባይ የሚሰማ የለም።*
*ፍርድን ድል ለመንሣት እስኪያወጣ፥ የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም*
*የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም። (ማቴ 12፥19-20)*

ኢየሱስ ከሮሜ መንግሥት ጋር እንዲፋለምላቸው አይሁድ የሚጠብቁትን አይነት ጦረኛ ንጉሥ አልነበረም፡፡ ይልቁኑ፣ እርሱ ጨዋና ርኅሩኅ ነበር፡፡

የብሉይ ኪዳኑን መግለጫ ለመጠበቅ፣ ኢየሱስን እንደ ድል አድራጊ ንጉሥና እንደ እግዚአብሔር ህዝብ ባለሥልጣን አስተማሪ ማቴዎስ ገልጦታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም፣ ኢየሱስ ትጉትና ርኅሩህ ንጉሥ መሆኑንም ማቴዎስ በአፅንዖት ገልጧል፡፡ ኢየሱስን በሕይወታችን እና በአገልግሎታችን እንድንከተል የቀረበልን ጥሪም ኢየሱስ በምሳሌነት ባሳየን መንገድ እውነትን እንድንናገር ይሞግተናል፡፡

ማቴዎስ የኢየሱስን መንግስትና ወንጌል ብሉይ ኪዳናዊ ቅርስ የገለጠልን በበርካታ መንገዶች ነው፡፡ በተመሳሳይም፣ ኢየሱስ ጥንታዊ ጥበቃዎች ሁሉ አብዛኛው ሰው ከሚጠብቀው በላይ ያሟላ መሆኑንም በአፅንዖት ገልጧል፡፡ መልካሙን የምሥራች፣ ወንጌሉን ግን እርሱ ፈፅሟል፡፡ መንግሥቱ፣ ህጉ፣ በተለይም ንጉሡ ራሱ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያትን በምድር ሲያመጣ ተፈፅመዋል፡፡

የኢየሱስን መንግሥትና ወንጌል ብሉይ ኪዳናዊ ቅርሶች ከተመለከትን፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ መሪ ሃሳብ ለማንሳት ዝግጁ እንሆናለን፡፡

# የእግዚአብሔር ህዝብ

አንደ ተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁሉ፣ በማቴዎስ ወንጌልም ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ህዝብ፣ የእግዚአብሔር የሆኑ፣ ሽልማት በውርስነት የተጠበቀላቸው፣ ንጉሡ የሚገዛቸው ልዩ ሕዝብ ናቸው፡፡ ከእግዚአብሔር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ የእርሱ ከሆኑት ከሌሎችም ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡

የእግዚአብሔር ህዝብ የተሰኘውን መሪ ሃሳብ በሦስት ክፍሎች እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ማቴዎስ ከቤተክርስቲያን ጋር ማዛመዱን፣ ሁለተኛ፣ "**የእግዚአብሔር ቤተሰብ**" በማለት መጥራቱን፣ ሦስተኛ፣ የእግዚአብሔር ህዝብ ከኢየሱስ የተቀበለውን ጥሪ፣ እንመለከታለን፡፡ ቤተክርስቲን የእግዚአብሔር ህዝብ ናት በሚለው ሃሳብ እንጀምር፡፡

## ቤተክርስቲያን

በብሉይ ኪዳን፣ እስራኤል የእግዚአብሔር ህዝብ ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን፣ የእግዚአብሔር ህዝብ አብዛኛውን ጊዜ "**ቤተክርስቲያን**" ተብለው ተጠርተዋል፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ "**ቤተክርስቲያን**" ለሚለው ቃል በዚህ ዘመን የምንጠቀምበት ቃል ኤክሌሺያ የሚለውን የግሪክ ቃል ነው፡፡ በሰብዓ ሊቃናት፣ ለብሉይ ኪዳኑ የግሪኩ ኤክሌሺያ ያገለገለው የእብራይስጡ ካሃል የተሰኘው ቃል ነው፡፡ ያም የብሉይ ኪዳኑ የእብራይስጡ ቃል ለጉባኤ ወይም ለእስራኤል ማኅበር የሚጠቀምበት ነው፡፡ የቃላት ሽግግሩም ከእስራኤሉ "**ጉባኤ**" ወደ ክርስቲያና "**ቤተክርስቲያን**" ተደርጓል፡፡ ይህም ኢየሱስም ሆነ ማቴዎስ የክርስቲያናን ቤተ ክርስቲያን የሚያዩዋት የእስራኤሏ ጉባኤ ቀጥይ አድርገው መሆኑን ይገልጣል፡፡

በብሉይ ኪዳን **“ማህበር”** የሚለው ቃል ወይም በእብራይስጡ ካሃል የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለበትን እንያዝ፡፡ በዘሌዋውያን 16፥33፤ በዘኁልቁ 16፥47፤ መሳፍንት 20፥2 እና በመዝሙር 22፥22 ውስጥ የእስራኤል ህዝብ **“ማህበር”** ተብለዋል፡፡ እርግጥም፣ የእግዚአብሔር ህዝብ ጉባኤ በብሉይ ኪዳን ወሳኝ ስፍራ የነበረው ሲሆን፣ ለቢዩ ኢዩኤል ለእስራኤል ከተጠቀመባቸው ስሞች መካከል አንዱ ሲሆን የእግዚአብሔር ህዝብ በመጨረሻው ዘመን የሚታደስ መሆኑን ሲተነብይ ተጠቅሞበታል፡፡ በኢዩኤል 2፥16 ውስጥ እንዲህ አውጇል፡

***ሕዝቡንም አከማቹ፥ ማኅበሩንም ቀድሱ፥ (ኢዩኤል 2፥16)***

በዚህ ጥቅስ የዕብራይስጥ ዋና ቅጂ ውስጥ፣ **“ማህበር”** የሚለው ቃል ትርጉም ካሃል ነው፡፡ በግሪኩ የሰብዓ ሊቃናት ቅጂ ውስጥ ግን፣ ኤክሌሺያ የሚለው ቃል በተለምዶ **“ቤተክርስቲያን”** ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

ማቴዎስ ይህንኑ ተመሳሳይ ቃል በማቴዎስ 16፥18 የኢየሱስን ቃል ሲዘግብ ተጠቅሞበታል፡

***በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ (ማቴ 16፥18)***

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ያስተጋባው በኢየሱስ ትንቢት ላይ ሲሆን ያንንም ቤተክርስቲያኔን እመሠርታለሁ ሲል ገልፆታል፣ ትርጉሙም የእርሱን ካሃል ወይም የመጨረሻውን ዘመን መሲሃዊ ማኅበር ማለት ነው፡፡

> ***ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ቤተክርስቲያኔን እመሠርታለሁ ብሏል፡፡ እንደማስበው ቤተክርስቲን ለሚለው ቃል የአዲስ ኪዳኑ የግሪኩ ቃል፣ ኤክሌሺያ፣ የብሉይ ኪዳኑን የእግዚአብሔር ህዝብ ማኅበር ሃሳብ የያዘውን ካሃል የተሰኘውን ቃል በእርግጥ የሚያስተላልፍ የግሪክ ቃል መሆኑን በማስታወስ መጀመር መልካም አጀማመር ነው፡፡ ስለዚህም የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን የብሉይ ኪዳኑ ማኅበር፣ የእግዚአብሔር ህዝብ ማኅበር ቀጣይ ነው ማለት ነው፡፡ [ቄስ ሚካኤል ግሎዶ]***

የማቴዎስ 16 ሁነት ኢየሱስ መሲሃዊ ንጉሥ እንደሆነ በመናገሩ ተቃውሞው እያደገ በመጣበት ወቅት የተከናወነ ነው፡፡ የዚህም ተቃውሞ አንድ ምክንያት ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ከእስራኤል ማኅበር ጋር በማጣቀስ ማበረታታቱ ነበር፡፡ እርሱ የፈለገው መሲሃዊቷን ማኅበር ወይም ቤተክርስቲያንን በመመሥረት እቅዱ እንዲተማመኑ ነው፡፡

የኢየሱስ ቃላት በተጨማሪም ቤተክርስቲያን የእርሱ መሆኗን ግልፅ አድርገዋል፡፡ የጴጥሮስ አይደለችም፡፡ የእስራኤልም አይደለችም፡፡ በአባሎቿ የተገዛች ዲሞክራሲያዊ ተቋምም አይደለችም፡፡ የመሲሁ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ በወንጌሉ መግቢያ ውስጥ መልአኩ ለዮሴፍ የተናገረውን ቃል ሲዘግብ ማቴዎስም ግልፅ አድርጎታል፡፡

በ1፥21 ውስጥ ማቴዎስ የመዘገበውን አድምጡ፡

**እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። (ማቴ1፥21)**

በዚህ ጥቅስ፣ ኢየሱስ ከመወለዱም አስቀድሞ፣ በማርያም ማህፀን ውስጥ ያለው ህፃን የእግዚአብሔር ህዝብ ሁሉ የእርሱ የሆኑለት መሲህ መሆኑን መልአኩ ለዮሴፍ አረጋግጦለታል፡፡ እርሱ ንጉሣቸው እነርሱም ህዝቡ ናቸው፡፡

> ***እናም እኛ በግላችን የኢየሱስ ተከታዮች ብቻ ሳንሆን፣ እኛ ኢየሱስ ከሙታን በመነሣቱ እና በመንፈሱ መሰጠት መቅደሱ ያደረገን አዲስ ፍጥረት አካላት ስነሆን፣ ስለዚህም እኛ ሰዎች ምህረትንና ይቅርታን የሚቀበሉባት፣ የጎደላቸውን መግቦት የሚያገኙበት እና ብቸኝነት ሲሰማቸውም ወዳጆችን የሚገኙባት የእግዚአብሔር መንግሥት በቤተክርስቲን ውስጥ የሚገለጥባቸው ህዝቡ ነን፡፡ እናም፣ ቤተክርስቲያን የአዲሲቷ ሰማይና ምድር ቅድመ ቅምሻ ስትሆን፣ አንድ ቀንም ለፍጥረት ሁሉ በይፋ ትገለጣለች፡፡ [ቄስ ሚካኤል ግሎዶ]***

የእግዚአብሔር ህዝብ ጫና ውስጥ ሲወድቁ፣ የሕወት ገጠመኞችም ወደታች ሲጎትታቸው፣ የጨለማውም ጥለቅት እስኪሰማቸው ድረስ ሲከብባቸው፣ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ **"ቤተክርስቲያኔን እመሠርታለሁ፡፡ መሲሃዊ ማኅበሬን እመሠርታለሁ፡፡"** እርሱ ንጉሣችን መሆኑንም አረጋግጦልናል፣ እርሱ በልቡናችን ያለ የተመረጠ ትርፋችን ነው እርሱ በመጨረሻም በእርግጠኝነት ያድነናል ይባርከናልም፡፡ በዚህኛው ሕይወታችን ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አንድ ቀን ይሆናል፡፡ በዚህም እርግጠኞች ነን፡፡

የእግዚአብሔርን ህዝብ እንደ ቤተክርስቲያን ከመግለጥ በተጨማሪ፣ ማቴዎስ የእግዚአብሔር ቤተሰብ በማለት ገልጿቸዋል፡፡

## የእግዚአብሔር ቤተሰብ

የማቴዎስ ወንጌል የእግዚአብሔር ህዝብ ከእግዚአብሔር እና እርስ በእርስ ያላቸውን ግንኙነት ለመግለጥ **"አባት"**፣ **"ልጅ"**እና **"ወንድም"** የመሳሰሉ የተለመዱ ቋንቋዎችን ከ150 ጊዜ በላይ ተጠቅሟል፡፡ ይህንን የመሰሉ የተለመዱ ቋንቋዎችን የተጠቀመ ወንጌል የዮሐንስ ወንጌል ነው፡፡ ዮሐንስ የተጠቀመው ግን፣ በኢየሱስና በሰማያዊ አባቱ መካከል ስላለው ግንኙነት ለማውሳት ነው፡፡

በተቃራኒው፣ ማቴዎስ ሲጠቀምበት ግን በእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከል ስላለው ግንኙነት ለማውሳት ነው፡፡ ስለ እግዚአብሔር ቤተሰብ ይናገርበታል፡፡ በተቀዳሚነትም፣ ማቴዎስ ቃላቶቹን ሲጠቀም እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚያደርገውን ክብካቤና ጥበቃ አፅንዖት ለመስጠት ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 6፥4፣ እግዚአብሔር ለህዝቡ የሚያደርገውን ክብካቤ ኢየሱስ እንዲህ ገልጦታል፡

> ***በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል። (ማቴ 6፥4)***

ይህንኑ ተመሳሳይ ቋንቋም በቁጥር 6፣ እንደገናም በቁጥር 18 ውስጥም ተጠቅሟል፡፡ ነጥቡም እግዚአብሔር ልጆቹን ለማበረታታትና ለመመገብ ግድ የሚለው መሆኑን ማሳየት ነው፡፡

ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ እንዴት ሊጸልዩ እንደሚገባ ሲያስተምራቸውም፣ በማቴዎስ 6፥8 ላይ መመሪያውን ሲሰጣቸው እንዲህ ብሏል፡

*ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና። (ማቴ 6፥8)*

የሚወድደን ሰማያዊ አባታችን ስለሆነ፣ እግዚአብሔር እንደሚባርከን፣ ጸሎቶቻችንን እንደሚሰማን፣ በእርግጥ እናውቃለን፡፡

*እኔ የማስተምረው በመንፈሳዊ ግንባታ አቅጣጫ ነው፣ እናም ስለ ጌታ ፀሎት ከማናገራቸው አንዱ መጻለይ ስንጀምር በየትኛዋም ደቂቃ ውስጥ ልክ እንደኛው የሚጸልዩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እውቅና ልንሰጥ ይገባል የሚል ነው፡፡ እግዚአብሔርን "አምላክ" ብለን የምንጠራበት አንዱ ምክንያት፣ እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ ጸሎቶች የሚሰማው አንድና ብቸኛ የእርሱን ትኩረት የሚሻ ልመና እንደሆነ አድርጎ የሚቆጥር በመሆኑ ነው፡፡ ያም ሁኔታ እኛን ወደ ተቀደሰ ህብረት፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ቤተሰብ ውስጥ ያስገባናል፡፡ ከዚያን በኋላ፣ የሚመጣው "አባት" የሚለው ቃል ነው፡፡ ስለዚህ ማንም ልሁን ወይም የትም ልሁን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር የምቀርበው አባ እያልኩ፣ እንደ አባቴ ነው ማለት ነው፡፡ እናም አንድ ሰው በፖላንድ ሆኖ እግዚአብሔርን "አባ" ብሎ ሲጠራ፣ እኔም በአሜሪካን እግዚአብሔርን "አባ" ብዬ ስጠራ፣ ወንድምና እህት ሆንን ማለት ነው፡፡ አንድ አባት ካለን፣ የአንድ ቤተሰብ አባላት ነን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ፣ እንደማስበው ማቴዎስ ይህንን ነገር ደግሞ ደጋግሞ ሲያነሳው የመንግሥተ ሰማያትን ፅንሰ-ሃሳብ በብርቱ ጨብጦታል ማለት ነው፡፡ እኔ በምጸልይበት በየትኛውም ሰዓት፣ እኔ የምናገረውን ተመሳሳይ ነገር ከሚናገሩ በርካታ ሰዎች ጋር የምጸልይ መሆኔን እንድረዳ፣ እናም እኔ የምለውን የሚሉ ከሆነ ደግሞ፣ ቤተሰብ መሆናችንን እንድናውቅ የሚደርገን የጸሎት ሕይወት ነው፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር]*

*እግዚአብሔር የእርሱ ቤተሰብ አባላት እንዳደረገን ከማወቅ የበለጠ የሚያበረታታ ነገር የለም፡፡ ይቅር መባል ትልቅ ነገር ነው፣ ሆኖም ጄ.አይ. ፓከር Knowing God በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደገለጡት ደግሞ፣ መጽደቅም ትልቅ ነገር ነው፣ ከሁሉ ይልቅ ግን የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆን ደግሞ ትልቅ ነገር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን አባትነት ማግኘት፣ በእውነት በሕይወታችን እጅግ አስደናቂው የእግዚአብሔር ሥራ ውጤት ነው፡፡ እኛ በአንድ ዳኛ ምህረትን የተቀበልን ብቻ አይደለንም፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ሆነናል፣ እርሱም አባታችን፣ እኛም ልጆቹ ሆነናል፡፡ ስለዚህም፣ እኛ፣ ከክርስቶስ ጋር ወራሾች ነን፡፡ ለኢየሱስ የሆነው ሁሉ፣ ያም ሁሉም ነገር፣ የእኛ ሆኗል፡፡ የእኛም ውርስ ሆኗል፡፡ የቁጣ ልጆች የነበርንበት፣ ውርሳችንም የእግዚአብሔር ቁጣ የነበረበት ወቅት ነበር፡፡ አሁን ግን ቁጣው ተወግዶልን፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ሆነናል፡፡ የልጅነትን ሥልጣን በመቀበላችን የመለኮታዊ ብህርይ ተካፋዮች በመሆን ከክርስቶስ ጋር ወንድሞች ተብለን ተጠርተናል፡፡ እንደ መርገም የነበረው ጽድቃችን ተወግዶ በክርስቶስ ጽድቅ ተገዝቶአል፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች*

*ስንሆን፣ ወደ እርሱ ቤተሰብ ተጠርተናል፡፡ ያም ከምናስበው እጅግ የላቀ ታላቅ በረከት ነው፡፡ [ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ]*

በማቴዎስ 6፥25-34፣ የእግዚአብሔር ልጆች የእርሱን ክብካቤ እንደሚያገኙ ለማረጋገጥ ኢየሱስ ሁለት ምሳሌዎችን ተጠቅሟል፡፡ **"ስለ ሰማይ ወፎች"**እና **"ስለ ሜዳ አበቦች"** በማንሳት፣ እግዚአብሔር ለጥቃቅን ፍጥረታቱ እንኳን እንደሚያስብ ተናግሯል፡፡ ነጥቡም፣ እግዚአብሔር ለእነዚያ ጥቃቅን ፍጥረታት የሚያስብ ከሆነ፣ ለገዛ ህዝቡማ ምንኛ ይበልጥ እንደሚያስብ ማሳየት ነው፡፡ ሰማያዊ አባታችን ለእኛ የተመረጠ ምግብ፣ ልብስና መጠለያን ያዘጋጅልናል፡፡

ኢየሱስ በተጨማሪም ደቀ መዛሙርቱን በአገልግሎት ስለሚጠብቃቸው ታላቅ ፈተና ባስጠነቀቀበት ወቅትም፣ የእግዚአብሔር አባታዊ ክብካቤና ጥበቃ እንደማይለያቸው በአፅንዖት ተናግሯል፡፡ ለምሳሌ፣ በ10፥19-20 ውስጥ፣ ኢየሱስ እንደሚታሰሩ ነግሯቸዋል፡፡ ሆኖም የአብ መንፈስ አብሯቸው እንደሚሆንም ነግሯቸዋል፡፡ በአገልግሎታቸው ምክንያት ሕይወታቸው አደጋ ሲገጥመው፣ አባታቸው እንደሚጠብቃቸው አስታውሷቸዋል፡፡

በማቴዎስ 10፥29-31 የኢየሱስን የማበረታቻ ቃላት አድምጡ፡

***ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም።***
***የእናንተስ የራሳችሁ ጠጕር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል።***
***እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ። (ማቴ 10፥29-31)***

*ለሚያምኑ ሰዎች፣ ክርስቲያን መሆን በራሱ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ በብዙ የዓለም ክፍሎችም በስደት ላይ ናቸው፡፡ በሕይወታቸው ደስ የሚሰኙበት ትልቁ ነገር የአካሏ ክፍል መሆናቸው፣ የእግዚአብሔር ህዝብ ተብለው መጠራታቸው ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር አባታችን መሆኑን ይነግሩናል፡፡ ሮሜ 8 እንደሚነግረንም፣ እግዚአብሔርን አባባ ብለን በመጥራታችን፣ አስደናቂ ዕድል ማግኘታችንን እናውቃለን፡፡ ዘወትርም እግዚአብሔር ስለ እኛ የሚያስብልን መሆኑንም እናውቃለን፡፡ እግዚአብሔር ለቤተሰቡ አባላት ፍቅርን እንደሰጠም እናያለን፡፡ እናም፣ ለሚያምን፣ በክርስቶስ አማካይነት እግዚአብሔር አሁን አባታችን ስለሆነ በልቡ የሚሰማው ታላቅ መበረታታት ነው፡፡ [ዶ/ር ጀፍ ሎውማን]*

የእግዚአብሔርን ህዝብ እንደ ቤተክርስቲያንና እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብነታቸው ካየን፣ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔርን ህዝብ ጥሪ እንመለከታለን፡፡

## ጥሪ

የእግዚአብሔር ህዝብ የእርሱ ቤተክርስቲያንና የእርሱ ቤተሰብ የመሆን ትልቅ ዕድል አግኝተዋል፡፡ እንደ እርሱ ህዝብ የተቀበልነው ጥሪ ግን መከራን፣ አደጋንና መንገላታትንም ይጨምራል፡፡ ኢየሱስ

ራሱም መከራን የተቀበለው መሲሃዊ ንጉሣችን ነው፡፡ እኛም እርሱን ስንከተል፣ መከራን እንቀበላለን፡፡

ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 10፥34-36፣ ጥሪያችን መጠላትም እንዳለበት ኢየሱስ ተናግሯል፡፡ እስኪ የተናገረውን አድምጡ፡

*በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም።*
*ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤*
*ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል። (ማቴ 10፥34-36)*

በማቴዎስ 16፥24-25 ደግሞ፣ በዚህ መንገድ አስቀምጦታል፡

*በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።*
*ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል። (ማቴ 16፥24-25)*

እርሱ እንደተጠላ የእርሱ የሆኑትም እንደሚጠሉ ኢየሱስ ያውቃል፡፡ ለንጉሣችን፣ መከራ የመከበሪያ መንገዱ ነው፡፡ ለእኛም ነገሩ እንዲሁ እውነትነት አለው፡፡

*ሰዎች በመስቀል ላይ ሲያዩት በውጊያው እንዳልቀናው ሊያስቡ ይችላ፣ በመቃብር ውስጥ ሲገባማ ከጨዋታ ወጪ እንደሆነ ያስባሉ፣ የዠንጉት ግን ስለ ሦስተኛዋ ቀን ማለዳ ነው፡፡ "ይህንን አካል ብታፈርሱት፣ በሦስተኛው ቀን አስነሣዋለሁ" በማለት ኢየሱስ ተናግሯል፡፡ ቤተክርስቲያንም እንዴት እንደ ተገለለች፣ እንደ ተነቀፈች፣ ከፋም እንደ ደረሰባት ሰናስብ፣ አየሱስ በወደ ማሳው ያስገባት ያቺው ቤተክርስቲያን ዛሬም በማሳው ላይ ያለችው የዘመኗ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ እንግዲህ በምን ዓይነት መከራ እንዳለፈችና እንደፀናች ተመልከቱ፡፡ አሁን ደግሞ ትቂት ዘለቅ እንበል፡፡ ስጋ ስለ ሆነው ስለ ክርስቶስ የሚነገረውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ሊገድሉት አልቻሉም፣ ዛሬም ሊገድሉት አይችሉም፡፡ ስለዚህ እኛም የገዢ የዕርሱ ቤተክርስቲያን አካላት ነን፣ እናም አንድም ነገር፣ የገሃነም ደጅ እንኳን እንዲያቆማት እና የእርሱን ተልዕኮ እንዲያደናቅፍ አይፈቅድም፡፡ ይህች ቤተክርስቲያን ተልዕኮ አላት፣ እናም ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ የጠፉትን እንድታመጣና ደቀመዛሙርትን እንድታፈራ ይጠበቅባታል፡፡ ታዲያ ያ ምንኛ ታላቅ ደስታ ነው! እኔና እናንተም አስተማማኝ ዋስትና አለን ደግሞም ቤተክርስቲያን እንደምትፀና ስለምናውቅ አሁንም እንኳን በእውን የትንሣኤ ልምምድ ውስጥ አለን፡፡ [ዶ/ር ዊሊ ዌልስ]*

የህዝቡ መከራ እንደሚያበቃ፣ ከችግሮቻችን እንደሚያሳርፈን፣ ሰላምንም እንደሚሰጠን እና በማይሰፈር ልክ እንደሚባርከን ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቶናል፡፡ ሆኖም ገና የሚሆን ነው፡፡ ተመልሶ

እስከሚመጣና ሁሉን አዲስ እስከሚያደርግ ድረስ፣ መከራን የተቀበለውን ንጉሣችንን ፈለግ መከተል ጥሪያችን ነው፡፡

*እርሱ የመጣው ሕይወት እንዲሆንልንና እንዲበዛልን መሆኑን ኢየሱስ ነግሮናል፡፡ ግን፣ እንደምታውቁት፣ በዚህ ዘመን፣ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ካወቅን በኋላ፣ አሁንም በመከራ፣ በስቃይና በህማም ውስጥ እናልፋለን ደግሞም እንሞታለን፡፡ ተስፋ እንቆርጣለን እንጓጓለንም፡፡ ዛሬም እንታወካለን እንዲያውም ሰቆቃ ይደርስብናል፡፡ ታውቃላችሁ፣ የተትረፈረፈ ሕይወት መቀበል ማለት እነዚህን ሁሉ እንደሚያካትት መረዳትና በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ውስጥ ክርስቶስ ከእኛ ጋር እንዳለ ማወቅ ማለት ነው፡፡ ካልታወክንና ተስፋ ካልቆረጥን በስተቀር በክርስትና ሕይወታችን ልናውቅ የሚገቡንን ነገሮች አናውቅም ነበር፡፡ ሰቆቃን ካልቀመስን ደግሞም ሃሴትንና ደስታን ካልቀመስን በምን እናውቃቸዋለን፡፡ በዚህ ስፍራ አንድ ዋና ነገር አለ፡፡ ኢየሱስ "እኔ የመጣሁት ሕይወት እንዲሆንላችሁ እና ያም ሕይወት የተትረፈረፈ እንዲሆን ነው" ብሏል፡፡ ሆኖም፣ ታውቃላችሁ፣ ገና አንድ ነገር እንናፍቃለን፡፡ "በክርስቶስ መሆን" ማለት እርሱ የሚያመጣውን ነገር ሁሉ ሙላቱን መናፈቅ ማለትም ጭምር ነው፡፡ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያኑ ተመልሶ የሚመጣባት ቀን አለች፡፡ አንድ ቀን ለሁሉ በሚታይ መንገድ ክርስቶስ ሁሉን ይገዛል፡፡ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክበት ምላስ ሁሉ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን የሚመሰክርበት ቀንም ይመጣል፡፡ እንባ ከዐይን የሚታበስበት ለቅሶም የማይኖርበትም ቀን ይመጣል፡፡ አሁን ለእኛ በክርስቶስ የተትረፈረፈ ሕይወት ማግኘት ማለት ሊመጣ ያለውን ነገር በመናፈቅ፣ በአሁኑ ሕይወት በወደቀው ዓለም ውስጥ የሚገጥመንን ስቃይም ሆነ ደስታ በመታገስ በክርስቶስ ማረፍ ማለት ነው፡፡ የተትረፈረፈ ሕይወት ማለት ተመልሶ እስከሚመጣ ድረስ በክርስቶስ መታመን ማለት ነው፡፡ [ዶ/ር አልበርት ሞህለር]*

# መደምደሚያ

በዚህ በማቴዎስ ወንጌል ጥናታችን፣ ከፀሐፊው ማንነት፣ ከቀደምት ተደራሲያኑና ከወቅቱ፣ አንፃር ዳራውን መርምረናል፤ ውቅርና ይዘቱንም መርምረናል ደግሞም የብሉይ ኪዳን ቅርሱን ዐበይት ርዕስ ሃሳቦችንና በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ የሰጠውን አፅንዖት አይተናል፡፡

የማቴዎስ ወንጌል በብሉይ ኪዳን ስለ መንግሥተ ሰማያት የተሰጡ ተስፋዎች በኢየሱስ በመሲሃዊው ንጉሥ ስብዕናና ሥራ አማካይነት የተፈፀሙበትን የምሥራች ያውጅልናል፡፡ መልካሙም የምሥራች ኢየሱስ መንግሥቱን በእኛ ውስጥና በእኛ አማካይነት የመሠረተና አሁንም የቀጠለ መሆኑ ነው፡፡ ይህ መልካም የምሥራች ግን ዘወትር ቀላል አይደለም፡፡ እንዳየነውም፣ መከራ የተቀበለውን መሲሃዊ ንጉሥ እንድንከተል የተቀበልነውንም ጥሪ ማቴዎስ በመሠረታዊ ሁኔታ ገልጦልናል፡፡ ግን በተጨማሪም፣ የሰማያዊ አባታችንንም በረከቶች እንዲሁ በመሠረታዊ ሁኔታ ገልጦልናል፡፡ በረከቶቹም ንጉሣችንን በታማኝነት እንድንከተለው፣ መንግሥተ ሰማያትም በሙሉ ክብሯ እስክትገለጥ ድረስ በመከራችንም ውስጥ ፅንተን እንድንጠብቀው የሚያስችሉን ናቸው፡፡